# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት







## በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት የተወረሱ ንብረቶች አያያዝ አጠባበቅ እና አወጋገድ በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

**ታህሳስ 2007**
**አዲስ አበባ**

# ማውጫ

ክፍል አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
የኢትዮጵያ ገቢዎች ናጉምሩክ ባለስልጣን ዓላማ፣ሥልጣን ናተግባር........ 2
የባለሥልጣን መ/ቤቱ ዓላማ ........ 2
የባለሥልጣን መ/ቤቱ ሥልጣን ናተግባር ........ 2
የባለሥልጣን መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል........ 4
ድርጅታዊ መዋቅር........ 4
የባለስልጣን መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ........ 5
የተወረሱ ንብረቶች አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድ የስራ ሂደት መግለጫ (Process descerption) ........ 6
የኦዲቱ አላማ........ 7
የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 7
ለኦዲቱ የተለየው የኦዲት አከባቢ ........ 7
የኦዲቱ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 8
የኦዲቱ መመዘኛመስፈርት ........ 8
ክፍል ሁለት ........ 9
የኦዲት ግኝት ........ 9
ሀ/የተወረሱ ንብረቶች መረጃ አያያዝ ሥርዓት ቀልጣፋና ውጤታማነትን በተመለከተ፣ ........ 9
የተወረሱ ንብረቶችን ለመመዝገብና ለማስወገድ የሚያግዝ ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት የተዘረጋና የመረጃ ቋት/data base/ የተዘጋጀ ስለመሆኑ፤ ........ 9
የተወረሱ ንብረቶች አመዘጋገብና እና የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መድረጉን በተመለከተ ........ 10
በባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶችን መረጃ በአግባቡ መያዙን እና በየበጀት አመቱ ቆጠራ የሚደረግ ስለመሆኑ ፣........ 12
ባለስልጣኑ የዋጋ መተመኛ ዘዴ /ሲዲ/ ወቅታዊ ማድረጉን በተመለከተ፣ ........ 14
ለ/ የተወረሱ ንብረቶች አያያዝና አጠባበቅ ኢኮኖሚያዊ እና ቀልጣፋ መሆኑን በተመለከተ፣ ........ 15
ለመድህኒት፣ ለምግቦችና ለአደገኛ ዕቃዎች መጋዘን ያዘጋጀ መሆኑ፣ ንብረቶች ይዞታቸውና መሰረታዊ ባህሪያቸው ሳይለወጥ እንዲጠበቁና ለቁጥጥር አመቺ በሆነ ሁኔታ የተቀመጡ መሆኑን በተመለከተ፣........
ባለስልጣኑ በቅ/ጽ/ቤቶች የሚወረሱ የውጭ አገር ገንዘቦች በተቀመጠው ጊዜ ገቢ ማደረጋቸውን ክትትልና ቁጥጥር ማድጉን በተመለከተ፣........ 20
የሚወረሱ ንብረቶች አጠባበቅና አወጋገድ በዕቅድ መያዙን እና በክንውን ላይ ለሚታዩ ክፍተቶች የመፍትሄ እርምጃ መውሰዱን በተመለከተ ........ 21
ባለስልጣኑ የአፈጻጸም መመሪያ አውጥቶ ለቅ/ጽ/ቤቶች ያሰራጨ፣ ክፍተቶች በመለየት እንዲሻሻሉ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣ 22
ባለስልጣኑ የተሟላ የሰው ሃይል ያለው መሆኑን በተመለከተ፣ ........ 23

ሐ/ በባለስልጣኑ መወገድ የሚገባቸው የተወረሱ ንብረቶች  የአወጋገድ ስርዓት ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋና ብቃት ባለው መልኩ ማድረጉን በተመለከተ፣.......... 24
በቅ/ጽ/ቤቶች የሚያዙ የከበሩ ማዕድናት ወደ ገቢ እንዲቀየሩ ማድረጉን በተመለከተ.......... 24
በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን የሚያስወግድ ኮሚቴ ማቋቋሙና ክትትል ማድረጉን በተመለከተ .......... 25
ቶሎ የሚበላሹ ዕቃዎች እና አደገኛ የሆኑ ንብረቶችን ወዲያውኑ እንዲወገዱና እንዲተላለፉ የተደረገ መሆኑን በተመለከተ፣.......... 27
ባለስልጣን መ/ቤቱ በሽያጭ የሚተላለፉ ንብረቶች ክፍያ  ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ .......... 28
በታክስ እዳ የተያዙ ንብረቶችን ወደ ገቢ እንዲቀየሩ መደረጉን በተመለከተ.......... 30
በድርድር ያልተሸጡ ዕቃዎች በጨረታ እንዲሸጥ የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ፣ .......... 31
ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በዱቤ የሚሻጣቸውን  እቃዎች ዝርዝርና  ዋጋ የሚያሳውቅ መሆኑን በተመለከተ .......... 32
መ/ ባለስልጣን መ/ቤቱ  የተወረሱ ንብረቶቸ አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድ ቅንጅታዊ  የአሰራር ስርዐት መዘርጋቱና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፣.......... 33
ከባለ ድርሻ አካላት ጋር የሚሰራበት ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱንና የመግባቢያ ሰነድ ያለው መሆኑን በተመለከተ.......... 33
ከአዲስ አበባ  ውጪ እና አዲስ አበባ የሚገኙ  ተሸከርካሪዎች  ለማስወገድ ከሚመለከታቸው ባድርሻ አካላት ጋር አብሮ የሚሰራ መሆኑን በተመለከተ .......... 33
ክፍል ሦስት .......... 35
የመደምደሚያ ሃሳቦች .......... 35
ክፍል አራት .......... 38
የማሻሻያ ሀሳቦች .......... 38
አባሪ 1፡ የመመዘኛ መስፈርት.......... i

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንለሀገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ ሚና ያለው ሲሆን፣ ገቢውን የሚሰበስበው ከሀገር ከሚገቡ፣ከሃገር ከሚወጡ ዕቃዎች ላይ ከሚጣል ቀረጥና ታክስ እንዲሁም ከተለያዩ የታክስ ዓይነቶች ነው፡፡
2. መቤቱ ከ1966 አብዮት በኋላ በነሐሴ 1967 ዓ.ም. የጉምሩክ ቀረጥና ኤክሳይዝ ታክስ አስተዳደር በመባል በአዲስ መልክ ተዋቀረ፡፡ የአለም ጉምሩኮች ሕብረት ምክር ቤት ያዘጋጀውን የንግድ ሸቀጦችን በተሰሩበት ንጥረ ነገር እና በአገልግሎታቸው የሚመድበውን የታሪፍ መጽሐፍ ከነሐሴ 1967 ዓ.ም.ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል ተደረገ፡፡
3. በ1989 ዓ.ም. በአዋጅ ቁጥር 60/1989 የፌዴራል መንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን በመባል እንደገና የተቋቋመ ሲሆን፣ ተጠሪነቱም ለገቢዎች ቦርድ እንዲሆን ተደነገገ፡፡ ከዚያም በአዋጅ ቁጥር 368/1995 የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ተጠሪነቱ ለገቢዎች ሚንስቴር ሆነ፡፡ በአዋጅ ቁጥር 587/2000 የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ "የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን" ተብሎ እንዲቋቋምና የባለስልጣን መ/ቤቱም ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲሆን ተደንግጓል፡፡
4. ከህጋዊ ንግድ ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ በአራቱም አቅታጫዎች የወጪ እና የገቢ ንግድ ህግን በመጣስ ዕቃዎችና ሸቀጦች ወደ ሀገር ይገባሉ ከሃገርም ይወጣሉ፡፡
5. በመሆኑም በንግድ ሥራ ክፍልና ንግዱን ሊያስፋፋ በሚችል የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ላይ አደጋዎችን ይጋርጣል፡፡ በሀገር ውስጥ በኮንትሮባንድ የሚገባውን ዓይነት ተመሣሣይ፡ ምርት የሚያመርቱ ፋብሪካዎች፣ የፋብሪካ ባለቤቶችን እና ነጋዴዎችን ከገበያ ያስወጣል፡፡ ሕጋዊ አምራቾችና ነጋዴዎች ሲከስሩ ሠራተኞች ከሥራ ስለሚፈናቀሉ በሀገሪቱ ላይ ሥራ አጥነት ይስፋፋል፡፡
6. የአገር ውስጥ ፋብሪካዎችና ማምረቻዎች ጥሬ ዕቃና ለምርት ግብዓትነት የሚያገለግሉትን መሣሪያዎች ለመግዛት አቅም ያጣሉ፡፡ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ኢንቨስትመንት ይዳከማል፡፡ መንግሥት ከገቢና ወጪ ንግድ ማግኘት የሚገባውን ቀረጥና ታክስ በማሳጣት በሀገሪቱ ለማስፋፋት የሚታቀደው የልማት ውጥን በአጭሩ ያስቀራል፡፡ እንዲሁም ጊዜ ባለፈባቸውና በተከለከሉ የመዋቢያና የመድኃኒት ምርቶች እንዲሁም የኬሚካል ውጤት የሕብረተሰቡ ጤና ይጓደላል፡፡

7. በመሆኑም በባለስልጣን መ/ቤቱ በቅ/ጽቤቶች በጉምሩክ መቆጣጠሪያ በኮንትሮ ባንድ በህገወጥ መንገድ ወደ ሀገር የሚገቡና የሚወጡ እንዲሁም በታክስ ዕዳ የሚወረሱ ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ መጠን ያላቸው የተለያዩ ንብረቶች በባለስልጣኑ በየጊዜው የሚወረሱ ቢሆንም ለነዚህ ንብረቶች ተገቢ የሆነ የንብረት አያያዝ/አመዘጋገብ፣ አጠባበቅ በማድረግ ንብረቶቹ ሳይበላሹና መሰረታዊ ይዞታቸውን ሳይለቁ የማስወገድ ስራ ተገቢውንትኩረት ሰጥቶ መስራት ላይ ችግሮች የሚስተዋሉ በመሆኑ ለእነዚህ ችግሮች ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል፡፡

# የኢትዮጵያገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዓላማ፣ሥልጣንና ተግባር

## ባለሥልጣን መ/ቤቱ ዓላማ

8. የባለሥልጣኑ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡
   - ዘመናዊ የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት በመዘርጋት ለተገልጋዮች ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት፣
   - ታክስ ከፋዩ ግዴታውን በፈቃደኝነት እንዲወጣ ማስቻል፣
   - ኮንትሮባንድንና የታክስ ማጭበርበርና ስወራን በመከላከልና በመቆጣጠር የታክስና የጉምሩክ ሕግጋትን ማስከበር፣
   - ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን የታክስ ገቢ በብቃትና በወቅቱ መሰብሰብ፣
   - የፌዴራልና የክልል ታክስ አስተዳደር ሥርዓቶች የተጣጣሙ እንዲሆኑ ለማድረግ ለክልሎች አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፡፡

## የባለሥልጣን መ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

9. <u>ባለስልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 587/2000 ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መካከል፡-</u>
   - በመስኩ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን መሠረት በማድረግ ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ይሰጣል፤ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት ለባለሀብቶች የተሰጡ የታክስና የቀረጥ ነፃ መብቶች በአግባቡ እንዲፈፀሙ ያደርጋል፤ ለታሰበው ዓላማ መዋላቸውን ይከታተላል፡፡
   - ግብር/ታክስ ከፋዮች በፍቃደኝነት ግብር/ታክስ የመክፈል ባሕልን እንዲያዳብሩ የግንዘቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች ተግባራዊ ያደርጋል፣
   - የጉምሩክና የታክስ ሕጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን አፈፃፀም ለማሻሻል የበለጠ አጽንኦት በመስጠትና ሌሎች ገቢዎች በአግባቡ እንዲሰበሰቡ ለማድረግ የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ያካሂዳል፣ በጥናትና ምርምሩ ውጤት መሠረት ፖሊሲዎችንና ህጎችን ያመነጫል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

- ለገቢና ወጪ ዕቃዎች ቁጥጥርና ለታክስ አወሳሰን የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ በመስኩ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች የተሟላ የስታትስቲክስ መረጃ ያጠናቅራል፤ እንደ አስፈላጊነቱም ለሌሎች አካላት ያሰራጫል፣
- የጉምሩክና የታክስ ሕጎችን በመጣስ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ይመረምራል፤ ይከሳል ይከራከራል፤ ይህንኑ ለማከናወን የራሱን ዐቃቤያነ ሕግና መርማሪዎች ቡድን ያደራጃል አፈፃፀማቸውን ይቆጣጠራል፣
- በጉምሩክ ወደቦች፣ በወሰን አከባቢዎች፣ እንዲሁም በሌሎች የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ማቋረጫ መስመሮች በኩል የሚገቡና የሚወጡ ዕቃዎችንና ማጓጓዣ ይፈትሻል፣ የጉሙሩክ ስነስርዓት ተፈጽሞ መግባታቸውና መውጣታቸውን ያረጋግጣል፣
- ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡትን ወይም ከሀገር የሚወጡትን ዕቃዎች እንቅስቃሴ የመቆጣጠር ኮንትሮ ባንድ የመከላከል ስራ በፌደራል ፖሊስ አማካኝነት እንዲካሄድ የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል፣ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል ህጉ በሚፈቅደው መሰረት ተገቢውን እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፣
- የጉምሩክና የታክስ ሕጎችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ በማናቸውም ሰው እጅ የሚገኙ ሠነዶችን ይመረምራል፤ ይይዛል፤ ዘመናዊ የዕቃዎችና የሠነዶች ምርመራ አገልግሎት ላብራቶሪ ያደራጃል፤ በጥቅም ላይ ያውላል፣
- በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የጉምሩክና የታክስ ወንጀሎችን የመመርመር፤ የመክሰስና ኮንትሮባንድን የመቆጣጠር እንዲሁም ታክስ የመወሰንና የመሰብሰብ ሥልጣኑን በሙሉ ወይም በከፊል ለክልል የፍትህ አካላትና ገቢ ሰብሳቢ አካላት በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤ ለአፈፃፀሙ ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣
- ወደ አገር የሚገቡ ወይም ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ ዕቃዎች የሚከማቹበትን ስፍራ ይወስናል፣ መጋዘን ያቋቁማል፣ የመጋዘን ፈቃድ ይሰጣል፣ የቀረጥ ነጻ መሸጫ ዕቃዎችን መደብሮች ይቆጣጠራል፣ ስለ ዕቃዎቹ አያያዝ ጥበቃ ቁጥጥር ያደርጋል፣ የሰጠውን የመጋዘን ፈቃድ ያግዳል፣ ይሰርዛል፣ የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፣
- የታክስና የጉምሩክ አስተዳዳርን በሚመለከት ውሎችንና ዓለምአቀፍ ስምምነቶችን ያደርጋል፣
- በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣንና ለጉምሩክ ባለሥልጣን ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፣

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## የባለሥልጣን መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰውኃይል

## ድርጅታዊ መዋቅር

10. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የዋናው መ/ቤት እና የቅ/ጽ/ቤቶች አደረጃጀትና መዋቅር አጠናቆ ከጥቅምት/2004 ዓ.ም. ጀምሮ ትግበራ ላይ ይገኛል፡፡

11. ተቋሙ በአንድ ዋና ዳይሬክተር የሚመራ ሲሆን፣ የሚከተሉትን 5 የስራ ዘርፎች ማለትም፡- የኦፕሬሽን ፕሮግራም ዲዛይንና ልማት ፣የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ማስተባበሪያና ድጋፍ ፣ የህግ ማስከበር ፣ የኮርፖሬት ፣የለውጥና ሞደርናይዜሽን ስራ ዘርፎች በምክትል ዋና ዳይሬክተሮች የሚመሩና ለዋና ዳይሬክተሩ ተጠሪ ሆነው እንዲደራጅና እንዲዋቀር ተደርጓል፡፡ እንደዚሁም 23 ዳይሬክተሮች፣ 30 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች፣ ሁለት ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች፣ 153 የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማክሮ ግብር ከፋዮች ወረዳዎች ጽ/ቤት እና ከአዲስ አበባ ውጪ ያሉ የታክስ መሰብሰቢያ ማዕከላት በ22 መቅረጫ ጣቢያዎች እና በ50 መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች በመያዝ ተደራጅቷል፡፡

12. በተመሣሣይ የዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤትን የሚመራ የጽ/ቤት ኃላፊ በዳይሬክተር ደረጃ የተዋቀረና የተደራጀ ሲሆን፣ በጽ/ቤቱም ሦስት የአማካሪዎች (የታክስና የጉምሩክ ጉዳዮች፣ የስትራቴጅክ ኢንተለጀንስ ጉዳዮች እና የኮሚዩኒኬሽንና የሰው ሃብት ልማት ጉዳዮች) የስራ መደብ እንዲሁም ለዋና ዳይሬክተሩ ተጠሪ የሆኑ የውስጥ ኦዲት አገልግሎት ዳይሬክቶሬት፣ የስነ-ምግባር መከታተያ ዳይሬክቶሬት፣ የሴቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት እና የኢንቨስትመንት ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት እንዲኖሩት ተደርጎ ተደራጅቷል፡፡

### የሰው ሀይል

13. በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የዋናው መ/ቤትና የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አደረጃጀትና መዋቅር መሠረት ከተፈቀደው አጠቃላይ የሥራ መደብ ብዛት 15,304. ሲሆን እስከ ሰኔ 2005 ዓ.ም ድረስ የተሸፈነ የሥራ መደብ ብዛት 8,391 (55 በመቶ) ፣ ክፍት የሥራ መደቦች ብዛት 6,913(45 በመቶ) ነው፡፡

## የባለስልጣን መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

14. የባለስልጣን መ/ቤቱ የገንዘብ ምንጭ ከመንግስት የሚመደበለት ለደመወዝ፣ ለሥራ ማስኬጃና ካፒታል በጀት እና ከተለያዩ ለጋሽ አካላት የሚያገኘው ገቢ ሲሆንበ2003፣ በ2004 እና በ2005 በጀት ዓመታት ለሚያከናውናቸው ተግባራት ማስፈጸሚያ መደበኛ በጀት እንደቅደም ተከተላቸው 595,614,423፣ 649,718,634 እና ብር 762,888,651 በድምሩ ብር 2,008,221,709 ከመንግሥት ፀድቆ ለሚተገብሯቸው ተግባራት ማስፈፀሚያ ከተመደበለት በጀት ውስጥ እንደቅደም ተከተሉ ብር564,163,943በ2004፣ 605,682,508 እናብር737,614,244 በድምሩ ብር1,907,460 696. በፐረሰንት ሲቀመጥ 95%፣ 93% እና 97% ስራላይ አውሏል፡፡

## የተወረሱ ንብረቶች አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድ የስራ ሂደት መግለጫ (Process descerption)

15. የተያዙና የተወረሱ ንብረቶች ዳይሬክቶሬት በስሩ በታክስ ዕዳ የተያዙና የተወረሱ ንብረቶች ቡድን፣በጉምሩክ የተያዙና የተወረሱ ንብረቶች ቡድን አስተዳደርና የተያዙና የተወረሱ ንብረቶች ገማችና አስወጋጅ ቡድኖችየሚገኙ ሲሆኑ፣

16. በታክስ ዕዳ የተያዙና የተወረሱ ንብረቶች ቡድን ከቅ/ጽ/ቤቶች በታክስ ዕዳ እንዲያዙ ወይም ርክክብ እንዲፈጸምባቸው የሚላኩ የንብረት ዝርዝር በኮምፒውተር እንዲመዘገቡና የንብረቶቹ መረጃ መመሟላቱ የህግና አስተዳደራዊ ሂደታቸው ያለቀላቸው መሆኑ ተጣርቶ መረጃውንፋይል ያደርጋል፣ንብረት ከመያዙ በፊት ያልተሟሉ ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተው እንዲመጡ ከዳይሬክቶሬቱ ጋር በመነጋገር ቅ/ጽ/ቤቶችን በደብዳቤ ያሳውቃል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር የንብረት ርክክብ ይፈጽማል፣ርክክብ የተፈጸመባቸው ንብረቶችን ለማጓጓዝ ከዳይሬክቶሬቱ ጋር በመነጋገር ቅድመ ሁኔታዎች እንዲሟሉ፣ወደ መጋዘን የገቡ ንብረቶች በአግባቡ እንዲደረደሩ እና ሊጓጓዙ የማይችሉ ንብረቶች ባሉበት እንዲጠበቁ ያደርጋል፣ርክክብ የተፈጸመባቸው ንብረቶች እንዲሸጡ/እንዲወገዱ ለአስወጋጅ ቡድኑ ያስተላልፋል፡፡

17. በጉምሩክ የተያዙና የተወረሱ ንብረቶች ቡድን በጉምሩክ የተተው፣የተያዙ በኮንትሮ ባንድ የተወረሱ ሸቀጦችን ለሶስተኛ ወገን የማስተላለፍ ጥያቄ ያቀርባል የሽያጭ ገቢ ይሰበስባል፣ ቅ/ጽ/ቤቶች ለጅንአድ እና ለአዲስ ፋና ያስረከቡትን ሞዴልና ድርጅቱ የተረከበበትን Merchandise receiving voucher(MRV)ይልካሉ፣የጉሙሩክ ዕቃ ማስረከቢያ ሞዴል 266 እና ጅንአድ ሸቀጥ መረከቢያ ደረሰኝ MRV ያመሳክራል፣ በርክክብ ሰነዱ መሰረት የሽያጭ ዋጋ ያዘጋጃል፣ ገንዘቡ ገቢ ስለመሆኑ ይከታተላል፣ ሂሳቡ መሰብሰቡን ለኦፊሰሩ ያሳውቃል፣ የሽያጭ ገንዘቡን ለቅ/ጽ/ቤቶች ያሳውቃል፡፡

18. የተያዙና የተወረሱ ንብረቶች ገማችና አስወጋጅ ቡድን በድጋሚ የቀረበውን ንብረት ዝርዝር ይፈትሻል፣የንብረት ዋጋ የሚተምን አካል በመምረጥ ያሰወስናል፣ የወቅቱን ገበያ አየተዘዋወረ ያጠናልከ2 በላይ ድርጅቶችን፣ በማወዳደር በቃለ ጉበኤ ተፈራርሞ ይይዛል፣ የንብረቱን የመነሻ ዋጋ ለቅርብ ኃላፊ አቅርቦ ያጸድቃል፣የጨረታ ሰነድ እንዲዘጋጅ ለቡድኑ ይመራል፣ኦፊሰሩ ገቢ የሆነውን የሽያጭ ገንዘብ ለሸየጭ ንብረት ላስረከበው ቅ/ጽ/ቤት ያሳውቃል፡፡

## የኦዲቱ አላማ

19. ኦዲቱ ዓላማ ባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶችን ለመያዝ፣ ለመጠበቅና ለማስወገድ የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ስርአት መዘርጋቱን እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል የአሰራር ስርአት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በመገምገም አፈፃፀሙ አጥጋቢ ሆኖ ካልተገኘ ያልሆነባቸውን ምክንያቶች ለይቶ በማውጣት የማሻሻያ ሃሳብ ለማቅረብና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

20. ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በኢትጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪ በናሙና ከተመረጡ ቅ/ጽ/ቤቶች መካከል የአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት፣ የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽቤት፣ ከምስራቅ አዲስአበባ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት፣ ከከፍተኛ ግብርከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ከአዳማቅ/ጽ/ቤት፣ ከሚሌቅ/ጽ/ቤት፣ ከድሬደዋ ቅ/ጽቤት፣ ከጅጅጋ ቅ/ጽቤትና ከጅምላ ንግድ አስመጪ ድርጅት/ጅንአድ/ የስራ ኃላፊዎች ጋር የኦዲት ቡድኑ ቃለ-መጠይቅ በማድረግ ከ2003 እስከ 2005 ዓ.ም ባለው ጊዜ በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶች አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድን በተመለከተ የተከናወኑ ስራዎችን የተመለከቱ መረጃዎችን በመከለስ፣ የስራ አፈጻጸሞችን በአካል ተገኝቶ በመመልከት፣ ለኦዲቱ የሚያስፈልጉ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በመተንተን የአለም አቀፍ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎችንና የኢትዮጵያ ክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች መሰረት በማድረግ የተከናወነ ነው፡፡

## ለኦዲቱ የተለየው የኦዲት አከባቢ

21. ከላይ የተመለከቱትን የኦዲት ዘዴዎች በመጠቀም የየተሰበሰቡትን መረጃዎች እና ማስረጃዎች መሰረት በማድረግ ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አከባቢ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በታክስ ዕዳና ጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶች አያያዝ አጠባበቅ፣ የመረጃ ስርዓት፣ መወገድ የሚገባቸው ንብረቶች የአወጋገድ ስርዓትና ከነዚህ ጋር የተያያዙ ስራዎችን

ከባለድረሻ አካላት ጋር ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ብቃት ባለው መልኩ ለማከናወን የሚያስችል ቅንጅታዊ አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ስለመደረጉ መገምገም፣ የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች

22. ከላይ በተገለጸው የኦዲት አከባቢ ስር አራት ዋና የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (audite ssue) ተለይተው ተቀምጠዋል፡፡ እነሱም፡-

1. የተወረሱ ንብረቶች መረጃ አያያዝቀልጣፋና ውጤታማ ስለመሆኑ ማረጋገጥ
2. የባለስልጣኑ የተወረሱ ንብረቶችን አያያዝና አጠባበቅ ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋና ብቃት ባለው መልኩ ስለማድረጉ መገምገም
3. በባለስልጣኑ መወገድ የሚገባቸው የተወረሱ ንብረቶች የአወጋገድ ስርዓት ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋና ብቃት ያለው ስለመሆኑ መገምገም
4. የባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶች አጠባበቅ፣ ሽያጭና አወጋገድን አስመልክቶ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የሚያከናውነው ቅንጅታዊ አሰራር ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑ መገምገም የሚሉ ናቸው፡፡

## የኦዲቱ መመዘኛመስፈርት

23. በኦዲት ቡድኑ የተመረጡ አራት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች እና ለመመዘን የሚረዱ (30) የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ፣ የተለያዩ መመሪያዎች፣ እና በባለስልጣኑ የተጠናው የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ሰነድ እና መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ በተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ላይ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የስራ ኃላፊዎች አስተያየት ሰጥተውበታል፡፡መመዘኛ መስፈርቱ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የኦዲት ግኝት

## ሀ/የተወረሱ ንብረቶች  መረጃ አያያዝ ሥርዓት ቀልጣፋና ውጤታማነትን በተመለከተ፣

### የተወረሱ ንብረቶች ለመመዝገብና ለማስወገድ የሚያግዝ ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት የተዘረጋና የመረጃ ቋት/data base/ የተዘጋጀ ስለመሆኑ፤

24. የባለስልጣኑ የመረጃ ቴክኖሎጂ  ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት በጉምሩክና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን ለመመዝገብና ለማስወገድ የሚያግዝ ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥርዓት ሊዘረጋ፣ የአሰራር ሥርዓቱን መደገፍ የሚያስችሉ ፕሮግራሞችና ሶፍትዌሮች በማበልጸግ ሥራ ላይ ሊያውልና የመረጃ ቋት (data base) ሊኖረው ይገባል፡፡

25. ይሁን እንጂ የባለስልጣኑ የመረጃ ቴክኖሎጂ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት በጉምሩክና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶች ለመመዝገብና ለማስወገድ  የሚያግዝ  ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥርዓት ያልዘረጋና የአሰራር ሥርዓቱን መደገፍ የሚያስችሉ ፕሮግራሞች ሥራ ላይ እንዲውሉ ያላደረገ ሲሆን  እንዲሁም የንብረቶቹን ሙሉ መረጃ ማለትም መቼ እንደ ተወረሱ፣ መቼ እንደ ተወገዱና ያልተወገዱ ንብረቶችን የሚገልጽ የመረጃ ቋት/ data base/ እንደሌለው ታውቋል፡፡

26. የኦዲት ቡድኑ በናሙና ካያቸው አዲስ አበባ ቦሌ ኤርፖርት፣ አቃቂ ቃሊቲ፣ ሚሌ፣ አዋሽ መቅረጫ ጣቢያ፣ ድሬደዋና ጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤቶችንብረቶች ተወርሰው ወደ  መጋዘን ሲገቡና እና በተለያየ መንገድ ሲወገዱ መረጃቸው በዘመናዊ መልኩ ተደራጅቶ የተያዘ አለመሆኑን ሰነድ በመከለስ ፣ ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና በምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

27. ስለሁኔታው የቅ/ጽ/ቤቶቹ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ  ሲመልሱ ኮምፒውተር ላይ የሚሰራ ባለሙያ እጥረት ያለባቸው መሆኑን ፣ የሶፍትዌር አለመኖሩንና ዕቃዎች በባህሪያቸው እና በዓይነታቸው ተለይተው የማይያዙ በመሆኑ በቢን እና  በአይቲ ለመያዝ አስቸጋሪ እንደሆነባቸው  ገልጸዋል፡፡

28. እንዲሁም ስለ ጉዳዩ የባለስልጣን መ/ቤቱ  የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ሲመልሱ በመረጃ ቴክኖሎጂ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት በዕቅድ ተይዞ እስከ ታህሳስ 30/2007 ለማጠናቀቅ አስፈላጊው የቅድመ ዝግጅት  ስራዎች  እየተከናወኑ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

29. ይሁን እንጂ ባለስልጣን መ/ቤቱ የመረጃ ቴክኖሎጂ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት በጉምሩክና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን ለመመዝገብና ለማስወገድ የሚያግዝ ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥርዓት ቀደም ብሎ ተዘርግቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ የተወረሱ ንብረቶችን የተሟላ መረጃ ለማግኘት እንዳይቻል በማድረጉ የተወረሱ ንብረቶችን የማስወገድ ስራው ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ በሆነ እና ተጠያቂነትን በሚያጠናክር መልኩ እንዳይከናወን አድርጓል፡፡

## የተወረሱ ንብረቶች አመዘጋገብና እና የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ

30. ባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ ዕዳና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶች ወደ መጋዘን ሲገቡ እና በተለያየ ስልት ሲወገዱ ተገቢውን መረጃ እና ማስረጃ ለመስጠት የሚያስችል ቀልጣፋ እና ውጤታማ የንብረት አመዘጋገብ እና ሂሳብ አያያዝ ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

31. በባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶች መጋዘን ሲገቡና በተለያየ መንገድ ሲወገዱ የንብረት አመዘጋገብ ስርዓት ያለ ቢሆንም በአሰራር ስርአቱ መሰረት ተግባራዊ የማይደረግ በመሆኑ በቅ/ጽ/ቤቶች ወጥ የሆነ የንብረት አመዘጋገብ እንደሌለ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

32. የኦዲት ቡድኑ በናሙና ካያቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መካከል በአዲስ አበባ ኤርፖርት፣ በሚሌ፣ በድሬደዋ፣ በጅጅጋ ፣ በአዳማ ቅ/ጽ/ቤቶች እና በአዋሽ ማስተባበሪያ ፣ በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶች የተተው፣ ባለቤት የሌላቸው፣ በዱቤ እና በጨረታ የሚሸጡ እንዲሁም ለሌሎች መ/ቤቶች የሚተላለፉና የሚወድሙ ተብለው እንደ ዓይነታቸው እና ባህሪያቸው ተለይተው የማይመዘገቡ ሲሆን የአዲስ አበባ ኤርፖርት፣ አቃቂ ቃሊቲ፣ አዳማ፣ ድሬዳዋና ጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤቶች ምን ያህል ንብረቶች እንደገቡና እንደወጡ የሚመዘገቡበት የንብረት መቆጣጠሪያ ካርድ እንደሌላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

33. የሂሳብ አያያዝን በተመለከተ በቅ/ጽ/ቤቶችና በዋናው መ/ቤት ንብረቶች በተለያየ መንገድ ሲወገዱ ሂሳባቸው በgeneral ledger እንዲሁም በተላለፈላቸው ድርጅቶች ስም እንደ ጅንአድና አዲስ ፋና እና ሌሎች መ/ቤቶች ስም ተቀጽላ ሌጀር /subsidary ledger/ /የሂሳብ ቋት/ ተከፍቶ አይመዘገብም፡፡

34. ቅ/ጽ/ቤቶች ለጅንአድና አዲስ ፋና በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን በዱቤ ሽያጭ ሲያስተላልፉ ለዋናው መ/ቤት ሂሳቡን የሚያሳውቁ ቢሆንም ዋናው መ/ቤት ግን ሂሳቡ ገቢ ሲደረግ ለቅ/ጽ/ቤቶች እንዲያውቁ አያደርግም፣

35. እንዲሁም በናሙና ከታዩት በአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት ተሽከርካሪ በሚያዝበት ጊዜ በማቆያ ሞዴል 270 ተመዝግቦ በሞዴል 265 ውርስ ሆኖ ገቢ ሳይደረግ በቀጥታ በሞዴል 266 ወጪ የሚደረግ ሲሆን በተጨማሪም ተሽከርካሪዎች ሲወረሱ ያላቸው እና የጎደላቸውን ዕቃ መረጃ የሚሞላበት የመረካከቢያ ሰነድ ያለ ቢሆንም በአቃቂ ቃሊቲ፣ አዳማ፣ ሚሌ፣ ድሬደዋና ጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤቶች በመረካከቢያ ሰነዱ መሰረት የተሽከርካሪ ርክክብ የማይፈጸም መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ሰነድ በመከለስ ቃለመጠይቅ በማቅረብ እና የቅ/ጽ/ቤቶችን አሰራር በአካል ተገኝቶ በመገምገም ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

36. ስለ ሁኔታው የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ሲመልሱ ንብረቶችን እንደገቡ መመዝገብ የማይቻል መሆኑን የፍርድ ሂደት ያለባቸው የፍርዱ ሂደታቸው ሲጠናቀቅ እና የሌላቸው ደግሞ በገቢ ደረሰኝ ከገቡ በኋላ የሚመዘገቡ መሆኑን ይህም በብዙ ቅ/ጽ/ቤቶች የሚከናወን መሆኑን ነገር ግን በአንዳንድ ቅ/ጽ/ቤቶች ችግሮች መኖራቸው ታውቆ በአጠቃላይ የመረጃ አያያዝ ችግርን ለመፍታት ከመረጃና ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ጋር በቅንጅት እየተሰራ የሚገኝ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

37. በተጨማሪም ንብረቶች በመዝገብና በኮምፒውተር ምን ያህል ዕቃ እንደወጣና እንደገባ እንደሚመዘገብ እና ቢንካርድን በተመለከተ መደርደሪያ ያለበት መጋዘን የተለጠፈ መሆኑን ነገር ግን መጋዘን በሌለበትና ግዙፍ ባልሆኑ ዕቃዎች ላይ አለመኖሩን ይህም መደርደሪያ ሲኖር የሚከናወን መሆኑን፤

38. በበጀት በሚተዳደሩ የመንግስት መ/ቤቶች ውስጥ የዱቤ ሽያጭ አመዘጋገብ ስርዓት የሚፈቅድ የአሰራር ስርዓት ባለመኖሩ መፈጸም ያልተቻሉ መሆኑን ነገር ግን በዱቤ የተላለፉ ንብረቶች በህጋዊ ሞዴል ርክክብ ሲፈጸም በዋናው መ/ቤት መረጃዎች በሶፍትና በሀርድ ኮፒ የሚመዘገብ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

39. የሂሳብ መጠየቂያ ለድርጅቶቹ ሲላክ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በግልባጭ እንዲያውቁት የሚደረግ መሆኑን ነገር ግን የተጠየቀው ገንዘብ ገቢ ሲሆን ገቢው በቅ/ጽ/ቤቶች ሳይሆን በዋናው መ/ቤት ስለሚመዘገብ መረጃውን ለቅ/ጽ/ቤቱ ማሳወቁ አስፈላጊነቱን እንደማያምኑበት ገልጸዋል፡፡

40. ንብረቶች በሞዴል 270 ተመዝግበው በሞዴል 265 ገቢ ሳይሆኑ በቀጥታ በሞዴል 266 ወጪ ማድረግ በአንዳንድ ቅ/ጽ/ቤቶች የነበረ ችግር መሆኑን እና ችግሩ ከታወቀ በኋላ ግን በገቢና ወጪ መመዝገብ መጀመሩን ገልጸዋል፡፡

41. እንዲሁም ተሽከርካሪን በተመለከተ ማስቀመጫ መጋዘን ባለመኖሩ ምክንያት ተረካቢዎቹ በሰነዱ መሰረተ የተሽከርካሪዎቹን አካል ቆጥሮ ለመረከብ በመስጋት የማይፈጸም መሆኑን በቃሊቲ ፣ በድሬደዋ እና በጅጅጋ የመጋዘን ችግርን ለመፍታት የመጋዘን ግንባታ ሥራ

እየተሰራ ሲሆን  በአጭር ጊዜ ውስጥ መጋዘን መስራት በማይቻልባቸው ደግሞ የጥበቃ ስራውን ከሚያከናውኑ  የፌደራል ፖሊሶች ጋር የተሽከርካሪ ርክክብ ፎርማት ተዘጋጅቶ ከተቋሙ ጋር ለመወያት በዝግጅት ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

42. ይሁን እንጂ  ማናቸውም  ወደ ውርስ መጋዘን የሚገቡ ንብረቶች በመዝገብ እና በኮፒውተር መመዝገብ እናዳለበት የጉሙሩክ መጋዘን መመርያ ቁጥር 40/2002 ተግባራዊ አለመደረጉ፤ በበጀት የሚተዳደሩ የመንግስት መ/ቤቶች በሂሳብ መግለጫቸው ላይ በተሰብሳቢ እና በተከፋይ መመዝገብ የማይቻል ቢሆንም በዱቤ የተሸጡ ንብረቶችን ሂሳብ ለመከታተል የሂሳብ ቋት/ ledger / በመክፈት መከታተልን የማይከለክል በመሆኑ በአጠቃላይ በንብረቶች ገቢና ወጪ እና የተሽከርካሪዎች ርክክብ ላይ በባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች የተሰጠው ምላሽ በኦዲቱ ወቅት ከታዩት ችግሮች አንጻር አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

43. በመሆኑም በታክስ ዕዳ እና በጉሙሩክ የተወረሱ ንብረቶች አያያዝ፣ አመዘጋገብ፣ እና በዱቤ የተሸጡ ንብረቶች ሂሳብ ክትትል ላይ ችግር በመኖሩ ንብረቶች ለብክነት እንዲዳረጉና እና መንግስት ማግኘት የሚገባውን ትክክለኛ ገቢ በወቅቱ እንዳያገኝ ያደርገዋል፡፡

## በባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶች መረጃ በአግባቡ መያዙን እና በየበጀት አመቱ ቆጠራ የሚደረግ ስለመሆኑ ፤

44. በባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶች በዱቤ የሚሸጡ፣ ለሌሎች መ/ቤቶች የሚተላለፉ፣ በጨረታ የሚሸጡ፣ በማውደም የሚወገዱና ሊወገዱ ያልቻሉ ንብረቶች በዓይነት፣ በመጠንና በብዛት  ተለይቶ ተገቢው መረጃ በአግባቡ መያዙን ክትትል ሊያደርግና ባለሙያዎች መርጦ በማዋቀር በየበጀት አመቱ የንብረት ቆጠራ ሊያደርግና የቆጠራ ሪፖርት እንዲቀርብ ሊያደርግ ይገባል፡፡

45. በባለስልጣን መ/ቤቱ በዱቤ የሚሸጡ፣ ለሌሎች መ/ቤቶች የሚተላለፉ፣ በጨረታ የሚሸጡና በማውደም የሚወገዱ የተወረሱ ንብረትቶች በዓይነት፣ በመጠንና በብዛት  ተለይተው መረጃቸው በተሟላ  እና በአግባቡ መያዛቸውን በተመለከተ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር እንደማይደረግ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

46. በኦዲቱ ወቅት በተካሄደው የዶክመንት ክለሳዎች፣ ለስራ ኃላፊዎች ከቀረቡ ቃለመጠይቆችና ከመስክ ግምገማዎች ለማረጋገጥ እንደተቻለው በባለስልጣን መ/ቤቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በርካታ ንብረቶች ሳይወገዱ ከአምስት እስከ አስር ዓመት ተከማችተው የሚገኙ ሲሆን የንብረቶች የተጠናቀረ መረጃ የሌለ መሆኑ እንዲሁም መቼ እንደተወረሱ እና የንበረቶቹ ዋጋ በገንዘብ ምን ያህል እንደሆነ የሚያመላክት መረጃ እንደሌላቸው ታውቋል፡፡ ንብረቶቹ ለምን ሊወገዱ እንዳልቻሉ  በተካሄደው ማጣራት ዋና ዋና ምክንያቶች ተብለው የተገለጹት

የዕቃዎችን አይነት ፣ የተሰራበትን ሀገር አለማወቅ  የዕቃዎቹን ዋጋ ለመተመን አስቸጋሪ መሆኑ በአጠቃላይ ንብረቶቹን አስመልክቶ የተሟላ መረጃ ማግኘት ባለመቻሉ ለዕቃዎቹ የሚዘጋጀው ዋጋ የተጋነነ የሚሆንበት ሁኔታ ስለሚፈጠር ገገር እንዳይኖራቸው እንደሚያደርግ ለማወቅ ተችሏል፡፡

47. በህግ ተይዘው ቶሎ ውሳኔ የማያገኙና ዋጋ የማይገኝላቸው ዕቃዎች መኖራቸው የሚታወቅ ቢሆንም ከእነዚህ ውስጥ ምን ያህል እቃዎች እንዳልተወገዱና ምን ያህል መጠን እንዳለቸው የሚገልጽ የተጠናከረ መረጃ እንዳልተዘጋጀ ታውቋል፡፡

48.  በተመሳሳይ መልኩ ጅንአድ በዋጋ ምክንያት አልወስድ ያላቸው ምንያህል ንበረቶች እንደሆኑ በመጠን እና በብር የተጠናከረ መረጃ ያልተዘጋጀ ሲሆን ለተባባሪ መስሪያቤቶች የሚተላለፉና በጨረታ የሚሸጡ ተብለው ዕቃዎችና ተሸከርካሪዎች ተለይተው እንዳልተያዙ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

49. እንዲሁም ስለተሸከርካሪዎች የሚገልጽ መረጃ  ማለትም መቼ እንደተወረሱና  ሲያዙ የነበራቸው እቃዎችን የሚያሳይ መረጃ ተጠናክሮ እንደማይያዝ ታውቋል፡፡

50. የኦዲት ቡድኑ በናሙና ካያቸው በጅጅጋ 38 ፣ በአዲስ አበባ ቃሊቲ 7፣ በአዳማ 3 በሚሌ 18 እና በድሬደዋ የተወሰኑ ተሸከርካሪዎች ዝርዝር መረጃ የሚገልጽ ማለትም  ታርጋ ቁጥር፣ የምርት ዘመን፣ ሞዴል፣ ሻንሲ ፣ ሞተርና ሞዴል ቁጥር እና የተወረሰበት ቀን  በአግባቡ ያልተመዘገበ ሲሆን እንዲሁም በርካታ ቁጥር ያላቸው ተሸከርካሪዋች በናሙና በታዩ ቅ/ጽ/ቤቶች ሳይወገዱ ጥሩ ባልሆነ ሁኔታ ተቀምጠው እንደሚገኙ ታውቋል፡፡

51. የባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ ዕዳና በጉምሩክ የተወረሱ ምን ያህል ንብረቶች እንዳሉ ለማወቅና ለመከታተል ከተለያየ የስራ ሂደት ባለሙያዎች መርጦ በማዋቀር በየበጀት አመቱ ወጥ በሆነ መልኩ የንብረት ቆጠራ የማያደርግ በመሆኑ የኦዲት ቡድኑ በመስክ ምልከታ በናሙና ካያቸው ከ 2003-2005 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ  የአዲስ አበባ  ኤርፖርት በ2003 ፣ አቃቂ ቃሊቲ በ2004  እና አዳማ ቅ/ጽ/ቤት በ2005 ዓ.ም አንዳንድ ጊዜ ብቻ ቆጠራ ያደረጉ ሲሆን ሚሌ ፣ ድሬዳዋ እና ጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤቶች የንብረት ቆጠራ አድርገው እንደማያወቁ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

52. ስለሁኔታው የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ሲመልሱ በአንዳንድ ቅ/ጽ/ቤቶች ችግሩ መኖሩ የሚታወቅ ሲሆን በቀጣይነት በየበጀት አመቱ ከተለያዩ የስራ ክፍሎች  በተወጣጡ ባለሙያዎች የሚቋቋም የቋሚ ንብረቶች ቆጠራ ኮሚቴ በሁሉም ቅጽ/ቤቶች  እንዲቋቋም በማድረግ የንብረት ቆጠራው ተግባራዊ እንደሚደረግ እና መረጃን በተመለከተ የሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ንብረቶች ሳይሆን በአንዳንድ ቅ/ጽ/ቤቶች  የተወሰኑ ንብረቶች መረጃ አያያዝ ድክመት ለረጅም ጊዜ  ሲንከባለል የመጣ ችግር ሲሆን ከ2006ዓ.ም

ጀምሮ ይህን ችግር ለመቅረፍና የመረጃ አያያዝን ለማሻሻል እንዲሁም ያዋጋ ትመና ላይ ያሉ ችግሮችን ለማስተካከል ተከታታይ ስልጠናዎችን በመስጠት በቅርበት እየሰራ የሚገኝ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

53. ጅንአድን በተመለከተ በዋጋ ውድነት ምክንያት የማይወስዳቸው ንብረቶች በጨረታ ስለሚሸጡ እና የጨረታ መነሻ ዋጋው በኮሚቴ ተጠንቶ ስለሚቀርብ መረጃ ያለ መሆኑን፣

54. ተሽከርካሪን በተመለከተ ችግሩ ከ10 እና 20 ዓመታት በፊት ጀምሮ የነበረና ሲንከባለል የመጣ በመሆኑ በአንዳንድ ቅ/ጽ/ቤቶች የተወሰኑ ተሽከርካሪዎች መረጃዎች ያለመኖር በተቋሙም የሚታወቅ መሆኑና በ2006 ዓ.ም ከ90 በላይ የተሽከርካሪዎችን መረጃ በማጣራት የተወረሱና በህግ ሂደት ላይ ያሉ በአጠቃለይ ከተወረሱት ውስጥ 383 ተሽከርካሪዎች እንዲወገዱ የተደረገ ሲሆን ወጥ የሆነ የመረጃ አያያዝ ለመፍጠርም ቅጾች ተዘጋጅተው ሰፊ የመረጃ ማሰባሰብ ሰራ እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

55. ይሁንእንጂ በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የሚወረሱ ንብረቶች መረጃ በዓይነት፣ በመጠንና በብዛት ተለይቶ ከተወረሰበት ጊዜ አንስቶ በአግባቡ ሙሉ መረጃው በአግባቡ እንዲያዝ ባለመደረጉ ንብረቶችን በወቅቱ ለማስወገድና ወደ ገቢ ለመቀየር እንቅፋት የፈጠረ መሆኑና እንዲሁም ንብረቶች በየበጀት ዓመቱ ቆጠራ ባለመደረጉ ምን ያልህል የተወረሱ ንብረቶች እንዳሉ ወቅታዊ መረጃ ማግኘት ስለማያስችል በተለያየ ምክንያት የሚጎድሉ ንብረቶችን ተገቢውን ክትትል በማድረግ መረጃ አግኝቶ ወቅታዊ እርምጃ ለመውሰድና ተጠያቂነት ያለው የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት አላስቻለም፡፡

### ባለስልጣኑ የዋጋ መተመኛ ዘዴ /ሲዲ/ ወቅታዊ ማድረጉን በተመለከተ፣

56. በባለስልጣኑ የተዘጋጀው የዋጋ መተመኛ ዘዴ /ሲዲ/ ወቅታዊ ሊሆን እና በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ወጥነት ያለው ዋጋ ሊተመን ይገባል፡፡

57. ባለስልጣን መስሪያቤቱ የተወረሱ ንብረቶችን ለማስወገድ የእቃዎችን ዋጋ ለመተመን የሚጠቅምበት የዋጋ መተመኛ ሲዲ በየጊዜው ወቅታዊ መሆን ያለበት ቢሆኑም ወቅታዊ የማይደረግ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሲዲ ዋጋ አተማመኑ የንብረተቹን ሁኔታ ያላገናዘበ የተጋነነ ዋጋ የሚተመንበት አሰራር በመኖሩ ምክንያት እቃዎቹ ሳይወገዱ ለረጅም ጊዜያት የተቀመጡበት ሁኔታ መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት የተወረሱ የተለያዩ ኤሌክትሮኒክስ እቃዎች በሲዲ ዋጋ አተማመን ችግር ምክንያት ከ5 ዓመት በላይ ሊወገዱ አለመቻላቸውን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል ፡፡

58. የኦዲት ቡድኑ ስለጉዳዩ ለቅ/ጽ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ የሲዲ ዋጋ አተማመን ዘዴ ችግር ያለበት መሆኑን ለችግሩ ዋናው ምክንያቱንም ሲዲ

ዋጋ ለመተመን የሚያገለግለው በዋናነት ለአዳዲስና ለመደበኛ ዕቃዎች መሆኑንና የሚያዙት የኮንትሮባንድ ዕቃዎች ደግሞ በህጋዊ መልክ የሚገቡ ዕቃዎችን መስፈርት የማያሟሉ ስለሆነ ዋጋ ለመተመን አስቸጋሪ ማድረጉን ገልጸዋል፡፡ የሲዲ ዋጋ ወቅታዊ የማይደረግባቸው ምክንያቶች ደግሞ የኔት ዎርክ ችግር በመኖሩ፣ በቅ/ጽ/ቤቶች ሲዲ በየጊዜው ወቅታዊ የማይደረግ በመሆኑ ፣ በባለሙያዎች የዕውቀት ማነስ ችግር መኖሩ ፣ የመረጃ ዳታ ቤዝ በአግባቡ አለመደራጀት እና የጠቋሚዎችን ዋጋ ከፍ ለማድረግ ሲባል ለዕቃዎች የተጋነነ ዋጋ የሚተመንበት ሁኔታ መኖሩን ገልጸዋል ፡፡

59. በተመሳሳይ መልኩ የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ሲመልሱ የጉሙሩክ የዋጋ መተመኛ ሲዲ የተዘጋጀው የተወረሱ እቃዎችን ለማስወገድ ሳይሆን የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ለመተመን እንደሆነና ሲዲን እንደ አማራጭ እንደሚጠቀሙበት ገልጸዋል፡፡

60. በባለስልጣኑ የዋጋ መተመኛ ዘዴ /ሲዲ/ ወቅታዊ እንዲሆን እና ተከታታይ የአቅም ግንባታ እና ድጋፍ ባለማድረጉ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በጉምሩክ ለተወረሱ ንብረቶች የተጋነነ ዋጋ እንዲተመን በዚህም ምክንያት ንብረቶች በወቅቱ እና በትክክለኛ ዋጋ እንዳይወገዱ እና ንብረቶች ለክምችትና ብልሽት እንዲዳረጉ አድርጓል፡፡

## ለ/ የተወረሱ ንብረቶች አያያዝና አጠባበቅ ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋ መሆኑን በተመለከተ፣

### የተወረሱ መድሀኒቶች፣ ምግቦችና አደገኛ ዕቃዎች አጠባበቅን በተመለከተ፣

61. ባለስልጣንመ/ቤቱ ለተወረሱ ንብረቶች / ለመድሀኒት፣ለምግብ፣ ለአደገኛና ለለሌሎች ዕቃዎች / እንደ አይነታቸውና ባህሪያቸው እንዲሁም ይዞታቸው ሳይለወጥ ተጠብቀው እንዲቆዩ ለማድረግ የሚያስችል የተሟላ መሳሪያ ያለው ዝግና ክፍት መጋዘን ሊያዘጋጅ እና ንብረቶች ለቁጥጥር አመቺ በሆነ ሁኔታ የተቀመጡ መሆናቸውን ሊከታተል እና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

62. ባለስልጣኑ በጉምሩክ እና በታክስ ዕዳ ለተወረሱ የተለያዩ ንብረቶች እስከ ሚወገዱ ድረስ እንደ እቃዎቹ ዓይነትና ባህሪይ ተለይተው መቆየት የሚችሉበት የተሟላ መሳሪያ ያለው ዝግና ክፍት መጋዘን ያላዘጋጀ፣ ንብረቶች በመጋዘን ውስጥ በሚቀመጡበት ጊዜ ይዞታቸውንና መሰረታዊ ባህሪያቸውን ሳይለቁ ለቁጥጥር አመቺ በሆነ ሁኔታ እንዲቀመጡ ያላደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ /ምስል 1 እና 2/፡፡



ምስል 1 እና 2 አዲስ አበባ ኤርፖርት መጋዘን በዓይነት ሳይለዩ መጋዘን ውስጥ ተቀላቅለው የተቀመጡ ዕቃዎችና መድሀኒቶች

63. የኦዲት በድኑ በመስክ ምልከታ ወቅት በናሙና ካያቸው በጅጅጋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በጉምሩክ የተወረሱ ብዛት ያላቸው ንብረቶች እንደ ዓይነታቸውና ባህሪያቸው ተለይተው የሚቀመጡበት በቂ የሆነ ደረጃውን የጠበቀ መጋዘን እና የዕቃ ማስቀመጫ መደርደሪያ የሌላቸው በመሆኑ በህግ ጉዳይ ከተያዙት ጋር ተቀላቅለው የሚቀመጡ ሲሆን እንዲሁም ዕቃዎች ለበርካታ ቀናት በተያዙባቸው ተሽከርካሪዎችላይ ተጭነው እንደሚቀመጡ ለማወቅ ተችሏል፡፡ (ምስል 3 እና 4፡፡)




ምስል 3 እና 4 በጅጅጋ መጋዘን ተከማችተው የሚገኙ ንብረቶች እና በተሽከርካሪ ተጭነው የሚገኙ ዕቃዎች

64. በተመሳሳይ መልኩ በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት የሚገኙ ንብረቶቹ እንደ አይነታቸው ማለትም መድሀኒቶች፣ ኬሚካሎች፣ ምግብ ነኮችና ሌሎች ዕቃዎች ሳይለያዩ በአንድ መጋዘን ውስጥ እንደሚቀመጡ ለመረዳት ተችሏል፡፡ እንዲሁም የውርስ መጋዘኖች የሚያስተናግዱት የተወረሱ እቃዎችን ብቻ ሳይሆን የህግ ጉዳይ ያለባቸውን እቃዎችም ተቀላቅለው የሚቀመጡ በመሆኑና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ውርስ ከሆኑ በኋላ እቃዎች ለባለቤቶቹ እንዲመለሱ የሚደረግበት ሁኔታ በመኖሩ እቃዎችን ለማስተዳደር አስቸጋሪ ከማድረጉ በተጨማሪ በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት የሚገኘው መጋዘን ደረጃውን

ያልጠበቀና ቅ/ጽ/ቤቱ ካሉት መጋዘኖች አንደኛው መጋዘን ጣራው ዝናብ የሚያስገባ በመሆኑ ንብረቶቹ እየተበላሹ መሆኑና እንዲሁም ንብረቶቹ ገቢ የሚደረጉበት ሞዴል 265 ደረሰኞች በዝናብ እንደተበላሹ ለማወቅ ተችሏል፡፡

65. በሚሌ ቅ/ጽ/ቤት የተወረሱ ዕቃች፣ ምግብነክ፣ መድሀኒቶች፣ ኬሚካሎችና ሌሎች ዕቃዎች በተለያዩ ኮንቴይነሮች ውስጥ ታሽገው ምቹ ባልሆነ አቀማመጥ እንደተቀመጡና በሙቀት ሊበላሹ የሚችሉበት ሁኔታ መኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

66. በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ የተወረሱ ልባሽ ጨርቆች በግቢው ውስጥ መሬት ላይ በብዛት ተጥለው በዝናብ የሚባላሹና እስከሚወገዱ ጊዜ ድረስ በስርዓት እንዲቀመጡ ያልተደረገ መሆኑና በአዳማ እና ድሬደዋ ቅ/ጽ/ቤቶች ደግሞ እንደ ዘይት እና ሌሎች ምግብ ነክ ዕቃዎች የሚቀመጡበት መጋዘን ንጽህናውን ያልጠበቀና የተከማቹት ንብረቶች መጋዘኑ ውስጥ ባለው ከፍተኛ አቧራ በመበላሸት ላይ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል/ምስል 5/፡፡



ምስል 5 በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት ንጹህ ባልሆነ መጋዘን ተከማችተው የሚገኙ የምግብ ዘይት

67. በአጠቃላይ በናሙና በታዩት ቅ/ጽ/ቤቶች መድሀኒቶች፣ አደገኛ ዕቃዎችና ምግብ ነክች እንደ ባህሪያቸው ከሌሎች ተለይተው የማይቀመጡ ሲሆን ተዝረክርከው ንጽህናው ባልተጠበቀና ለአይጦች እና ለብልሽት በተጋለጠ ሁኔታ የሚቀመጡ መሆኑ ታውቋል፡፡

68. በሌላ በኩል አዲስ አበባ ቃሊቲ ፣ተሽከርካሪዎች ተለይተው የተቀመጡ ቢሆንም ለረጅም ግዜ ሳይወገዱ በዝናብ፣ በፀሀይ፣ በአቧራ መሰረታዊ ባህሪያቸውንና ይዞታቸውን እየለቀቁና ሳር በቅሎባቸው የሚገኙ ሲሆን እንዲሁም ድሬደዋ ቅ/ጽ/ቤት የተወሰኑ ተሽከርካሪዎች እና በጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤት የተወረሱ ተሽከርካሪዎች ይዞታቸው በፀሀይ፣ በዝናብና በቧራ እየተበላሸ የሚገኝ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ በመስክ ጉብኝት ተመልክቷል፡፡

69. በባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች የሚወረሱ ንብረቶች ወደ መጋዘን ሲገቡ እንደ አይነታቸውና ባህሪያቸው ተለይተው ለደህንነታቸው ተስማሚና ለቁጥጥር አመቺ በሆነ ሁኔታ የተቀመጡ አይደሉም፡፡ እንዲሁም በናሙና በታዩት ቅ/ጽ/ቤቶች ንብረቶቹ ተይዘው ወደ ውርስ መጋዘን ከገቡ በኋላ ወቅታዊ የሆነ ውሳኔ የማያገኙ በመሆኑ በተለይ በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ከፍተኛ የሆነ ክምችት የሚገኝ መሆኑ ፡፡ / ምስል 6 / እና /ምስል 7 /



ምሰል 6 በአዲስ አበባ ቃሊቲ በፀሀይ እና በዝናብ እየተበላየሚገኙ ተሽከርካሪዎ



ምስል 7 በአዲስ አበባ ቃሊቲ ሳይወገድ የቆየ ተሽከርካሪ ሳር በቅሎበት

70. በተጨማሪም በአዲስ አበባ ኤርፖርት፣ በአዳማ፣ በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ፣ በሚሌ፣ በድሬደዋና በጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤቶች በህግ ተይዘው ጉዳያቸው ያላለቀና ውሳኔ ያላገኙ ንብረቶች ከተወረሱት ጋር አንድላይ ተቀላቅለው በመጋዘን የሚቀመጡ መሆኑና በአዲስ አበባ ቃሊቲ፣ በሚሌና በጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤቶች የተወረሱ ተሽከርካሪዎች ጉዳያቸው በህግ ከተያዘ

ተሽከርካሪዎች ጋር ተቀላቅለው የሚቀመጡ መሆናቸውን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡
፡

71. በባለስልጣኑ ስር ከሚገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች መካከል በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው የታዩ የቅ/ጽ/ቤት የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጉዳዩን አስመልክተው በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ ንብረቶችን እንደ ዓይነታቸውና እንደባህሪያቸው ለማስቀመጥ ሙሉ ግብዓት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ መጋዘን የሌላቸው መሆኑንና መጋዘኖቹም ተገቢውን ትኩረት ተሰጥቷቸው ባለመስራታቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

72. ስለሁኔታው የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ የመጋዘን ችግር በአንድ ጊዜ የሚቀረፍ ሳይሆን ደረጃ በደረጃ የሚፈታ ችግር መሆኑንና በአቃቂ፣ በቃሊቲ በድሬደዋና በጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤቶች በዕቅድ ተይዞ የግንባታው ስራ እየተሰራ መሆኑንና ከድሬደዋ ቅ/ጽ/ቤት በስተቀር በሌሎች ቅ/ጽ/ቤቶች የመኪና ማቆሚያ መጋዘን የሌለና ችግሩን በኪራይ ለመፍታት ተሞክሮ የተሽከረካሪ ማቆሚያ መጋዘን ሊገኝ ባለመቻሉ ባለስልጣን መ/ቤቱ ከኮሚት ጋር በመነጋገር ባገኘው መሬት መጋዘን ለማሰራት የዲዛይን ስራ መጀመሩን፣ እንዲሁም የሚሌ የመጋዘን ሃላፊው በሙስና በመባረሩና በመታሰሩ ምክንያት የንብርት ርክክብ ባለመደረጉ መጋዘኑን መጠቀም ባለመቻሉ የተከሰተ ችግር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

73. በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ በቢሮ ለውጥ ምክንያት በአንድ ወቅት ተፈጥሮ የነበረና ከ 6 ወር በፊት የተቀረፈ ችግር መሆኑን ፣ የአዳማ እና የድሬደዋ ቅ/ጽ/ቤቶች ከአከባቢው ሁኔታ ጋር ሲታይ የተሸለ ቢሆንም ዘመናዊ የንብረት ማስቀመጫ ያለመኖር ችግር መኖሩ እንደሚታወቅና በመፍትሄው ላይም ዋናው መ/ቤት ከቅ/ጽ/ቤቶች ጋር በቅንጅት እየተንቀሳቀሰ መሆኑንና ፣ የንብረት አያያዝ ችግርን ለማስተካከል ባለፈው አመት ከካይዘን ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር ለቅ/ጽ/ቤቶች ስልጠና መሰጠቱን ገልጸዋል፡፡

74. በተመሳሳይ መልኩ ስለ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ባለስልጣኑ ለመድሀኒት፣ ለምግብ፣ ለአደገኛና ለሌሎች ዕቃዎች እንደ ዕቃዎቹ ዓይነትና ባህሪ ተለይተው የሚቀመጡበት የተሟላ መሳሪያ ያለው መጋዘን አለመኖር ፣ የመጋዘን ጥበት፣ ስራውን በሚፈለገው ደረጃ ለማከናወን የሚያስችል በጀት አለመኖርና ስራውን ለማከናወን ሰራተኛ የማግኘት ችግርያለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ኬሚካሎች እና መድሀኒቶች አወጋገድን በተመለከተ ደግሞ በሀገር ውስጥ ወይም በውጭ ሀገር ለማስወገድ ጉዳዩ የሚመለከተውን አካል ለይቶ ያለማወቅ ችግር መኖሩን ገልጸዋል፡
፡

75. ይሁን እንጂ በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ የታየው ችግር ከስድስት ወር በፊት እንደተፈታ የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ይገለጹ እንጂ የኦዲት ቡድኑ በግንቦት 2006 ዓ.ም የመስክ ምልከታ ባደረገበት ወቅት ችግሩ ያልተፈታ ሲሆን ከላይ በዝርዝር በተጠቀሱት ቅ/ጽ/ቤቶች መድሀኒቶች፣ ኬሚካሎች፣ አደገኛና ሌሎች ንብረቶች እንደ ዓይነታቸውና እንደ ባህሪያቸው ተለይተው መሰረታዊ ባህሪያቸውንና ይዞታቸውን ሳይለቁ ለቁጥጥር አመቺ በሆነ ሁኔታ እንዲቀመጡ ባለመደረጉ በአከባቢና በማህበረሰብ ላይ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል ሲሆን ንብረቶቹም በወቅቱ ተወግደው ወደ ገቢ እዳይቀየሩ ተጽዕኖ በማሳደር ላይ ይገኛሉ፡፡

## በቅ/ጽ/ቤቶች የሚወረሱ የውጭ አገር ገንዘቦች በተቀመጠው ጊዜ ገቢ ስለመደረጋቸውና ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ፣

76. በቅ/ጽ/ቤቶች የሚወረሱ የውጭ አገር ገንዘቦች በባለስልጣኑ በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ያሉ ዕቃዎች አወጋገድ መመሪያ ቁጥር 56/2003 መሰረት በ48 ሰዓት ውስጥ ለባለስልጣኑ ገቢ መደረጋቸውን ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

77. ይሁን እንጂ ባለስልጣን መ/ቤቱ በተለያዩ የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች በህገወጥ መንገድ ከሀገር ሲወጡና ሲገቡ የሚወረሱ የውጭ ሀገር ገንዘቦች በ48 ሰዓትውስጥ ከተያዙበት ቅ/ጽ/ቤት በወቅቱ ገቢ ስለ መደረጋቸው አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር እንደማያደርግ በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

78. የኦዲት ቡድኑ በመስክ ምልከታ በናሙና ተመርጠው ከታዩት ቅ/ጽ/ቤቶች በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ የተወረሰ ስድስት ሺህ (6000) የአሜሪካን ዶላር እና 3000 የሳውዲ ሪያል ከአራት ወር በላይ ገቢ ሳይደረግ በመቅረጫ ጣቢያው የሚገኝ ሲሆን ለባለስልጣኑ በወቅቱ ገቢ አልተደረገም፡፡

79. በባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ በቅ/ጽ/ቤቶች በህገ ወጥ መንገድ ወደ ሃገር ሲገቡና ሲወጡ የሚያዙ የውጭ ሀገር ገንዘቦች በወቅቱ ገቢ የሚደረጉ ቢሆንም አልፎ አልፎ የሚዘገዩበት ሁኔታም መኖሩን ገልጸው በመመሪያው በተገለጸው ጊዜ ገቢ ሳያደርጉ የሚዘገዩበት ምክንያት የገንዘቡን ምንጭ የማጣራት ስራ እና የነበረውን አሰራር ባለማወቅ በወቅቱ ገቢ የማይደረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

80. ስለሁኔታው የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ሲመልሱ አንዳንድ ቅ/ጽ/ቤቶች ከቦታ መራቅ እና በተለያዩ ችግሮች ምክንያት በወቅቱ ገቢ ያለማድረግ ችግርና አልፎ አልፎ ከቦታ ርቀት የሚከሰት መሆኑን በተጠቀሰው የአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ የነበረው የውጭ ሀገር ገንዘብ ግን ከአምስት ወር በፊት ገቢ መደረጉን

እንዲሁም ለወደፊቱ የሚያዙ ገንዘቦች በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ገቢ ለማድረግ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

81. ሆኖም ግን የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ገንዘቡ ከአምስት ወር በፊት ገቢ እንደተደረገ ይገለጽ እንጂ የኦዲት ቡድኑ የመስክ ምልከታ ባደረገበት ወቅት እስከ ግንቦት 2006 ዓ.ም ድረስ ገንዘቡገቢ ያልተደረገ መሆኑን ማስረጃ በመከለስና እና በቃለመጠይቅ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

82. በመሆኑም ባለስልጣን መ/ቤቱ በቅ/ጽ/ቤቶች የሚወረሱ የውጭ ሀገር ገንዘቦች በተቀመጠላቸው የግዜ ገደብ ውስጥ ገቢ እንዲሆን ተገቢውን ክትትል ባለመደረጉ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቱ ለብልሹ አሰራር እና ለምዝበራ እንዲጋለጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## የሚወረሱ ንብረቶች አጠባበቅና አወጋገድ በዕቅድ መያዙን በክንውን ላይ ለሚታዩ ክፍተቶች የመፍትሄ እርምጃ መውሰዱን በተመለከተ

83. ባለስልጣን መ/ቤቱ በጉምሩክ እና በታክስ እዳ ለሚወረሱ ንብረቶች አያያዝ ፣ አጠባበቅ እና አወጋገድ እስትራቴጅክ ዕቅድ ሊያዘጋጅ፣ እቅዱን መሰረት አድርጎ ዓመታዊ ዕቅድ ሊያዘጋጅና ዕቅዱን ተግባራዊ በማድረግ የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ሊያቀርብና በአፈጻጸም ላይ የታዩ ክፍተቶችን በመለየት የመፍትሄ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

84. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተካሄዱ የዶክሜንት ክለሳዎችና ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር ከተካሄዱ ቃለመጠይቆች ለማረጋገጥ እንደተቻለው ባለስልጣን መ/ቤቱ በጉምሩክ እና በታክስ እዳ የተወረሱ ንብረቶች አጠባበቅ እና አወጋገድን በእስትራቴጅክ ዕቅዱ የማያካትት ፣ አስትራቴጂክ እቅዱን መሰረት አድርጎ ዓመታዊ ዕቅድ የማያቅድ እና ዕቅዱን ተግባራዊ በማድረግ የዕቅድ ክንውን ሪፖርት የማያዘጋጅ ሲሆን እንዲሁም በአፈጻጸም ላይ ለሚታዩ ክፍተቶች የመፍትሄ እርምጃ እንደማይወስድ ለማረጋገጥ ተችሏል፡

85. ስለጉዳዩ የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ መቤቱ ቀደም ብሎ የችግሩን ስፋትና መጠን ተረድቶ ለስራው በሰጠው ትኩረት መሰረት እራሱን የቻለ አደረጃጀት እንዲኖረው ዳይሬክቶሬት በማቋቋም ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነት የተቀረጸለት ሲሆን ከተቋሙ ስትራቴጂክ አንጻር የራሱን አመታዊ ዕቅድ በ2006 ዓ.ም በማዘጋጀት ተግባራዊ በማድረግ የሚታዩ የአሰራር ክፍተቶችን በመለየት የመፍትሄ ሃሳባ ያቀርባል በማለት ገልጸዋል፡፡

86. ይሁን እንጂ በጉሙሩክ እና በታክስ አዳ የተወረሱ ንብረቶች አያያዝ ፣ አጠባበቅ እና አወጋገድ በእስትራቴጅክ ዕቅድ ባለመካተቱ፣እና እቅዱን መሰረት አድርጎ ዓመታዊ ዕቅድ ባለመዘጋጀቱ በአፈጻጸም ላይ የታዩ ክፍተቶችን በወቅቱ በመለየት የመፍትሄ እርምጃ እንዳይወሰድና በአጭር በመካከለኛና በረጅም ጊዜ መፈታት የሚኖርባቸውን ሀገራዊና

ተቋማዊ የትኩረት አቅጣጫዎችንና የመፍትሄ ሃሳቦችን በመለየት ለመንቀሳቀስ እንዳይቻል አድርጓል፡፡

**የባለስልጣን መ/ቤቱ የአፈጻጸም መመሪያ አውጥቶ ለቅ/ጽ/ቤቶች ያሰራጨ፣ ክፍተቶች በመለየት እንዲሻሻሉ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣**

87. ባለስልጣን መ/ቤቱ የመቋቋሚያ አዋጁን መሰረት በማድረግ የአፈጻጸም መመሪያ ሊያወጣ፣ ለቅ/ጽ/ቤቶች ሊያሰራጭ እና ተግባራዊ መደረጉን ሊያረጋግጥ እንዲሁም በአፈጻጸም ላይ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት እንዲሻሻል ሊያደርግ ይገባል፡፡

88. ባለስልጣን መ/ቤቱ የመቋቋሚያ አዋጁን መሰረት በማድረግ በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን አወጋገድ የአፈጻጸም መመሪያ ያወጣ እና ለቅ/ጽ/ቤቶች ያሰራጨ ቢሆንም በአፈጻጸም ላይ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት መመርያው እንዲሻሻል እንዳላደረገ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር ከተካሄዱ ቃለመጠይቆች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

89. በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን በተመለከተ የሚወገዱበትን አሰራር የሚገልጽ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተዘጋጀው መመሪያ ለሚመለከታቸው ቅ/ጽ/ቤቶች ወጥ በሆነ መልኩ ያላሰራጨና በመመሪያው መሰረት ተግባራዊ ስለመደረጉ በቂ ክትትል እና ቁጥጥር አልተደረገም ፡፡

90. በባለስልጣኑ ስር ከሚገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች መካከል በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው የታዩ የቅ/ጽ/ቤቶች የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ ጉዳዩን አስመልክተው በሰጡት ምላሽ፣የአዳማ እና የድሬደዋ ቅ/ጽ/ቤቶች በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶች የሚያሰወግዱበት መመሪያው ያልደረሳቸው መሆኑን በመግለጽ በመመሪያው መሰረት ወደ ገቢ እየተቀየረ እንዳልሆነና የባለ ዕዳ ድርጅቶችንተጠያቂ በማድረግ ለረጅም ጊዜ ክፍያዎች የሚፈጸምመሆኑን እንዲሁምበዋናው መ/ቤት ንብረቶቹን እንዲያስወግድ በዳይሬክቶሬት ደረጃ እንዲቋቋም የተደረገ ቢሆንም በንብረት አወጋገድ ዙርያ በዳይሬክቶሬቱ እና በቅ/ጽ/ቤቶች መካከል ስላውየሥራ ደርሻ ግልጽ የሆነ ግንዛቤ የሌላቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

91. የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ መመሪያ ቁጥር 56/2003 በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ያሉ ዕቃዎች አወጋገድ ሥርዓት መመሪያ የማሻሻያ ስራ በህግ ባለሙያዎች እየተሰራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

92. እንዲሁም በታክስዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን በተመለከተ ከዋናው መ/ቤት በ09/03/2001 ዓ.ም ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች የተላከ ሲሆን የተባለው ችግር በሂደት ተጣርቶ እንዲስተካከል ይደረጋል በማለት ገልጸዋል፡፡

93. ይሁንእንጂ በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶች አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድ መመሪያው ያልደረሳቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መኖራቸው እና በመመሪያው አፈጻጸም ላይ ያጋጠሙ ችግሮች ተለይተው በወቅቱ እንዲሻሻሉ ባለመደረጉ የመመርያዎች ተፈጻሚነትን ውጤታማ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡

**የባለስልጣን መ/ቤቱ የተሟላ የሰው ሃይል ያለው መሆኑን በተመለከተ፣**

94. በባለስልጣን መ/ቤቱ እና በቅ/ጽ ቤቶች በጉምሩክ እና በታክስ እዳ የተወረሱ ንብረቶችን ለማስተዳደርና ለማስወገድ የሚያስችል መዋቅሩን መሰረት ያደረገ የተሟላ የሰው ሃይል ሊኖራቸው ይገባል፡፡

95. በለስልጣን መ/ቤቱና በቅ/ጽ /ቤቶች በጉምሩክና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን ለመያዝ፣ ለመጠበቅና ለማስወገድ የሚያስችል መዋቅሩን መሰረት ያደረገ የሰው ሀይል እንዳልተሟላላቸው በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

96. በዋናው መ/ቤት የተያዙና የተወረሱ ንብረቶች ዳይሬክቶሬት በመዋቅሩ መሰረት 70 የሰው ሀይል የሚያስፈልገው ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በባለስልጣኑ ከቀረበው ማስረጃ በስራ ላይ የሚገኘው የሰው ሀይል 14 ብቻ ሲሆን እንዲሁም በባለስልጣኑ ስር ከሚገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች መካከል በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩ የቅ/ጽ/ቤቶቹ የስራ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ለኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ በአዲስ አበባ አቃቂ ቃሊቲ ፣ በአዲስ አበባ ቦሌ ኤርፖርት፣ በአዳማ፣ በሚሌ፣ በድሬደዋና በጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤቶች የተወረሱ ንብረቶችን ለመጠበቅና ለማስወገድ በመዋቅሩ መሰረት የተሟላ የሰው ሀይል የሌላቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

97. የባለስልጣን መ/ቤቱየበላይኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ጉዳዩን አስመልክተው በሰጡት መልስ የሰው ኃይል ችግርን ለማቃለል ሰፊ የቅጥር ሥራበዋናው መ/ቤት እና በቅ/ጽ/ቤቶች እየተከናወነ እንደሚገኝና የሚታየው ችግርም በየጊዜው በሚያጋጥም የሰው ኃይል ፍልሰት የተከሰተ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

98. በጉምሩክና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን ለመያዝ ለመጠበቅና ለማሰወገድ መዋቅሩን መሰረት ያደረገ የተሟላ የሰው ሀይል ባለመኖሩ የንብረት አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድ ሥራ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዳይከናወን አድርጎታል፡፡

## ሐ/ በባለስልጣኑ መወገድ የሚገባቸው የተወረሱ ንብረቶች የአወጋገድ ስርዓት ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋና ብቃት ባለው መልኩ መከናወኑን በተመለከተ፣

### የባለስልጣን መ/ቤቱ በቅ/ጽ/ቤቶች የሚያዙ የከበሩ ማዕድናት ወደ ገቢ እንዲቀየሩ ማድረጉን በተመለከተ

99. በቅ/ጽ/ቤቶች የተያዙ የከበሩ ማዕድናትበተያዙ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ገቢ ሊደረጉና ወደ ገቢ ሊቀየሩ ይገባል፡፡

100. በተለያዩ ቅ/ጽ/ቤቶች የሚያዙ የከበሩ ማዕድናት በተያዙ በአምስት የስራ ቀን ውስጥ ለባለስልጣኑ ገቢ ተደርገው ወደ ገቢ እንዲቀየሩ መደረግ ቢኖርባቸውም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት ቅ/ጽ/ቤቶችና ቃለመጠይቅ ከተደረገላቸው የስራ ኃላፊዎች ለማረጋገጥ እንደተቻለው በቅ/ጽ/ቤቶች የሚያዙ የከበሩ ማዕድናት በመመሪያው በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንደማይቀየሩ ታውቋል፡፡

101. የኦዲት ቡድኑ በናሙና ካያቸው ቅ/ጽ/ቤቶች አዲስ አበባ ኤርፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ምንነታቸው ያልታወቀ 55 ኪ.ግ የተወረሱ የከበሩ ማዕድናት ከአምስት አመት በላይ የተቀመጠ ሲሆን እንዲሁም መጠናቸው ያልታወቀ መዕድናት በቅ/ጽ/ቤቱ የሚገኙ ሲሆን ለሚመለከታቸው አካላት እንዲተላለፉ እና ወደ ገቢ እንዲቀየሩ አልተደረጉም፡፡

102. እንዲሁም በህገ ወጥ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት እና ለማስወጣት ሲሞከር የተያዙ 69,571.5 ግራም ከብርየተሰሩ ጌጣጌጦች እና የተለያ ሜታሊክ ሜርኩሬዎች ባለስልጣኑበኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተከራየቸው 4 የአደራ ማስቀመጫ ሳጥኖች ውሰጥ ከተቀመጡ ረጅም ጊዜያትን ስላስቆጠሩ ይዞታቸው እተቀየረ መሆኑን እንዲሁም በዳይሬክቶሬቱ የሚገኝ 146.3 ግራም የብር ጌጣጌጥ ወደ ገቢ እንዲቀየር እና ገንዘቡ በወቅቱ ገቢ እንዲሆን አልተደረገም፡፡

103. የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ሲመልሱ የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት የከበሩ ማዕድናት ወደ ዋናው መ/ቤት ገቢ ማድረግ ሳያስፈልግ ቅ/ጽ/ቤቱ መጨረስና ማስወገድ ያለበት ሲሆን ምንነቱ ያልታወቀው የከበረ ማዕድንን በተመለከተ ለማዕድንና ኢነርጂ ሚንስቴር ደብዳቤ ጽፈው እየተጠባበቁ መሆኑን እንዲሁም ከብር የተሰሩ ጌጣጌቶችና ሜታሊክ ሜርኩሪዎችን በቅርቡ በጨረታ ለመሸጥ የሰነድ ዝግጅት ሥራው መጠናቀቁን ገልጸዋል፡፡

104. ይሁንእንጂ በቅ/ጽ/ቤቶች የሚወረሱ  የከበሩ ማዕድናት በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለባለስልጣኑ ገቢ ባለመደረጋቸው መሰረታዊ ባህሪያቸውና ይዞታቸውን ሊለቁ ፣ ለብክነትና ለምዝበራ ሊጋለጡ እና መንግሰት ማግኘት የሚገባወን ገቢ በወቅቱ እንዳያገኝ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

## የባለስልጣን መ/ቤቱ በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን የሚያስወግድ ኮሚቴ ስለመቋቋሙና ክትትል ስለማድረጉ በተመለከተ

105. በባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን የሚያስወግድ ኮሚቴ ሊያቋቁም እና አፈጻጸሙን ሊከታተል ይገባል፡፡

106. የባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶችን የሚያስወግድ ኮሚቴዎች ከተለያዩ የስራ ሂደቶችና ባለድረሻ አካለት በማካተት ያቋቋመ ቢሆንም ኮሚቴው ተሰጠውን ተግባርና ሀላፊነት በአግባቡ እየተወጣ ስለመሆኑ ባለስልጣን መ/ቤቱ አስፈላጊውን ክትትል እና ቁጥጥር  እያደረገ እንዳልሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

107. በባለስልጣኑ የተቋቋመው ኮሚቴ በተለያዩ ጊዜያት የተያዩ እቃዎቸን ያስወገደ ቢሆንም የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በተሟላ ሁኔታ ከመወጣት አንጻር ለሌሎች መ/ቤቶች የሚተላለፉ ንብረቶች ላይ ትኩረትና ክትትል በማድረግ  ንብረቶቹ ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ እንዲተላለፉ አላደረገም፡፡

108. የኦዲት ቡድኑ በናሙና መርጦ በግንቦት 2006 ዓ.ምየመስክ ምልከታባደረገባቸው አዲስ አበባ ኤርፖርት፣ አዲስ አበባ ቃሊቲ፣ አዳማ፣ ሚሌ፣ ድሬደዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እናአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ ብዛት ያለቸው መድሀኒቶች፣ ኬሚካሎች፣ ቅርሶች እና የህክምና መገልገያ መሳሪያዎችእንዲወገዱ ሳይደረግከ 2 ዓመትእስከ 7 አመት ተቀምጠውየሚገኙ መሆኑን እንዲሁም ኤሌክትሮኒክሶች ፣ ሞባይሎች ፣ ተሸከርካሪዎች እና ሌሎች ዕቃዎች በወቅቱ እንዲወገዱ አለመደረጉን በቅ/ጽ/ቤቶቹ ከተከለሱ ሰነዶችና፣ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ቃለመጠይቅ በማቅረብ እና በካል ንብረቶቹን ተዘዋውሮ በመመልከት ንብረቶቹ ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ እንዲተላለፉ አለመደረጉን ለማወቅ ተችሏል ፡፡






ምስል 8 በአዳማ ያልተወገዱ ኤሌክትሮኒክሶች ምስል 9 በአዲስ አበባ ኤርፖርት የሚገኙ ያልተወገዱ የህክምና መሳሪያና ኬሚካሎች

109. የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ስለሁኒታው ሲመልሱ ለሌሎች መ/ቤቶች ሊተላለፉ የሚገባቸውን በርካታንብረቶች እንዲተላለፉ ፣ ተቃጥለው ሊወገዱ የሚገባቸው እንዲቃጠሉ መደረጉን እና በተለይ መድሀኒቶች በ2006 ዓ.ም ከመድሃኒትና ቁጥጥር ባለስልጣን እና ከጤና ጥበቃ ሚኒስተር ጋር በመሆን በአቃቂ ቃሊቲና አዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽቤቶች የሚገኙትን ከ 15 ቢ.ያጆ /15 መኪና ጭነት/በላይእንዲወገድ መደረጉን እንዲሁም በአዲስ አበባ ቦሌ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት የነበሩትን ጥቅም ላይ የሚውሉ የህክምና መሳርያዎችን ሙሉ በሙሉ ለቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ፣ ቅርጻቅርጾችን እና መጻሓፍቶችን ለባህልና ቱሪዝም እንዲተላለፉ መደረጉን እንዲሁም በሌሎች ቅ/ጽቤቶች ሰፊ ሥራ በ2006 ዓ.ም የተሰራ መሆኑን እና ቀሪውን በያዝነው ዓመት ለማከናወን በእቅድ መያዙን ገልጸዋል፡፡

110. በሌላ በኩል በኦዲት ቡድኑ ለባለስልጣን መ/ቤቱየሚመለከታቸውየሥራ ኃላፊዎች ከላይ የተገለጹትን ችግሮች አስመልክቶ በ06/01/07 ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ የንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ ከተለያዩ የስራ ሂደቶች የተወጣጣ መሆኑን ነገር ግን መደበኛ ስራው ሌላ በመሆኑ ንብረት የማስወገድ ሥራን ደረቦ የሚሰራ በመሆኑ ሥራውን በባለቤትነት የማይሰራ ሲሆን በሌላ በኩል ንብረቶቸ ለሚመለከተው አካል እንዲተላለፉ ቢጠየቅም የሚመለከታቸው አካላት ምላሽ ያለመስጠት ችግር መኖሩእንዲሁም ንብረቶችን ለማስወገድ በባለቤትነት የሚመለከተውን አካል ለይቶ የማወቅ ችግር መኖሩን ገልጸዋል፡፡

111. ይሁንእንጂ አስወጋጅ ኮሚቴው ንብረቶችን ለማስወገድ ያጋጠሙትን ችግሮች ለመፍታት ያደረገውን ጥረትና የወሰደውን የመፍትሄ እርምጃ የተወገዱትንና ሊወገዱ ያልቻሉ ንብረቶችን አስመልክቶ ለበላይ ኃላፊዎች በወቅቱ የማያሳውቅ በመሆኑ ንብረቶች ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ በወቅቱ እንዳይወገዱ ያደርጋል፡፡

**በአጭር ጊዜ የሚበላሹ ዕቃዎች እና አደገኛ የሆኑ ንብረቶችን በአፋጣኝ ሁኔታ እንዲወገዱና እንዲተላለፉ የተደረገ መሆኑን በተመለከተ፣**

112. የባለስልጣን መ/ቤቱ በአጭር ጊዜ የሚበላሹ ዕቃዎች፣ የቁም እንስሳትና አደገኛ የሆኑ የተወረሱ ንብረቶችን በአፋጣኝ ሁኔታ ሊወገዱና በባለስልጣን መ/ቤቱ ሊወድሙ የማይችሉ አደገኛ ወይም የተከለከሉ ዕቃዎችን ለማውደም ብቁ ለሆኑ መ/ቤቶች ሊያስተላልፍ ይገባል፡፡
113. ባለስልጣኑ በአጭር ጊዜ የሚበላሹ እና አደገኛ የሆኑ የተወረሱ ንብረቶችን በአፋጣኝ ሁኔታ እንዲወገዱ ያላደረገ እና በባለስጣኑ ሊወድሙ የማይችሉ አደገኛ ወይም የተከለከሉ ዕቃዎች እንዲወድሙ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካለት በወቅቱ እንዲተላለፉ እንዳላደረገ በኦዲቱ ወቅት ከተካሄዱ የዶክሜንት ክለሳዎች፣ ከስራ ኃላፊዎች ጋር ከተካሄዱ ቃለመጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡
114. በቅ/ጽ/ቤቶች ሊወድሙ የማይችሉ የተለያዩ አደገኛና የተከለከሉ እቃዎች ሲኖሩ ለማውደም ብቁ ለሆኑ መስሪያ ቤቶች እንዲወስዱዋቸው በተለየዩ ግዜያት ደብዳቤዎች የተጻፉ ቢሆንም ነገር ግን ደብዳቤዋች ይጻፉ እንጂ እቃዎቹ ለ አመታት ሳይወገዱ መጋዝን ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፡-
115. የኦዲት ቡድኑ በናሙና ካያቸው አዲስ አበባ ቃሊቲ፣ ድሬ ደዋና ሚሌ ቅ/ጽቤቶች መድሀኒቶች፣ ኬሚካሎች፣ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች መወገድ ባለባቸው መንገድ ቶሎ ያልተወገዱ ሲሆን፣ እንዲሁም በሚሌ፣ ድሬደዋና ጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤቶች በአጭር ጊዜ የሚበላሹ ምግብ ነክ የሆኑ ነገሮች ወዲያውኑ እንዲወገዱ ያልተደረገ ሲሆን እንዲሁም በአዲስ አበባ ቦሌ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት መድሀኒቶች፣ ኬሚካሎች፣ አደገኛ የሆኑ ተቀጣጣይ ነገሮችና ጥይቶች ለሚመለከታቸው አካለት እንዲተላለፉ አልተደረገም፡፡ (ምስል 10 እና 11)






**ምስል 10 በአዲስ አበባ ኤርፖርት ሳይወገዱ ለረጅም ጊዜ የተቀመጡ መድሀኒቶችና ኬሚካሎች**

116. የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ስለጉዳዩ ሲመልሱ አንዳንድ ኬሚካሎች በሀገር ውስጥ የማይወገዱ በመሆኑ ለረጅም ዓመታት ተቀምጠው እንደሚገኙ ይሁንና በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ስር ለሚገኘው ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በደብዳቤ ተጠይቆ መልስ ያልሰጠ መሆኑን እና አሁንም ጥረት እየተደረገ እነደሚገኝ እንዲሁም ተቀጣጣይ ነገሮችንና ጥይቶችን ለሚመለከተው መ/ቤት አሳውቀው መልስ እየተጠባበቁ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

117. ይሁን እንጂ ቶሎ የሚባላሹ አደገኛ የሆኑ ተቀጣጣይ ነገሮች እና በባለስልጣኑ ሊወገዱ የማይችሉ ሌሎች ንብረቶች ወዲያውኑ ለሚመለከታቸው አካላት በማሳወቅ በፍጥነት እንዲወገዱ የማይደረግ መሆኑ በአከባቢና በህብረተሰብ ጤና ላይ ጉዳትና አደጋ ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡

### ባለስልጣን መ/ቤቱ በሽያጭ የሚተላለፉ ዕቃዎች ክፍያ ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ

118. ባለስልጣን መ/ቤቱ በሽያጭ ለሚተላለፉ ወይም ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች በክፍያ ለሚረከቧቸው ዕቃዎች ተገቢውን ክፍያ በወቅቱ ለባለስልጣኑ ገቢ መደረጉን ሊከታተል እና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

119. ባለስልጣን መ/ቤቱ በዱቤ ሽያጭ ለሚተላለፉ ወይም ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች በክፍያ ለሚረከቧቸው ዕቃዎች ተገቢውን ክፍያ በወቅቱ ለባለስልጣኑ ገቢ ስለማድረጋቸው ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር እንደማያደርግ በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

120. ባለስጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶችን ከሚያስወግድበት መንገድ አንዱ በዱቤ ሽያጭ ሲሆን በዚሁ መሰረት ከጅንአድ እና አዲስ ፋና ድረጅቶች ጋር ውል በመግባት ንብረቶችን የሚያስተላልፍ ቢሆንም ፣ ነገር ግን ክፍያው በውሉ መሰረት ገቢ ስለመደረጉ ወይም ስለመሰብሰቡ አሰፈላጊውን ክትትል እና ቁጥጥር አላደረገም፡፡

121. ለጅንአድ በዱቤ ሽያጭ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ የተላለፉ እቃዎች እስከ ነሀሴ 2006 ዓ.ም በውሉ አንቀጽ ሦስት ንኡስ አንቀጽ 3.4 መሰረት በ120 ቀን ውስጥ መከፈል የነበረበት ብር 343,205,205.36 እና ከአዲስ ፋና ከ2005 ዓ.ም እስከ ነሀሴ 2006 ዓ.ም ብር 311,293.30 ያልተሰበሰበ ሲሆን እንዲሁም በወሉ አንቀጽ ሦስት ንኡስ አንቀጽ 3.5 መስረት በወቅቱ ገቢ ካልተደረገ በሀገሪቱ ከፍተኛ የወለድ መጠን መሰረት ይከፈላል የሚል ቢሆንም ተግባራዊ እንዳልተደረገ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

122. በድሬ ደዋ፣ ጅጅጋ ፣ ሚሌና አዳማ ቅ/ጽ/ቤቶች ለመከላከያ የሚሸጡ ምግብ ነክ የሆኑ እቃዎች በድርድር ሽያጭ የሚሸጡበት አሰራር ያለ እና በዚሁ መሰረት ገቢውን የሚሌ ቅ/ጽ/ቤት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሰስ የሚያደርግ ሲሆን የድሬዳዋ፣ የጅጅጋና የአዳማ

ቅ/ጽ/ቤቶች ግን የሚሰበስቡትን ገቢ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሰስ የማያደርጉና ለዋናው መ/ቤትም የማያሳውቁ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

123. የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ ቤቶች፡በዱቤ ሽያጭ በሚያከናውኑበት ወቅት በሪፖርት የሽያጩን ዋጋ ለዋናው መ/ቤት በደብዳቤ የሚያሳውቁ ቢሆንም ያሰወገዱዋቸውን ንብረቶች ሂሳብ ሌጀር ከፍተው የማይመዘግቡ ሲሆንዋናው መ/ቤትም ቅ/ጽ/ቤቶች የሚያሳውቁትን በዱቤ ሽያጭ የወሰዱ ድርጅቶችን ሂሳብ የሂሳብ ቋት / Ledger /በመክፈት ምን ያህል እንደተከፈለና ምን ያህል እንዳልተከፈለ ተገቢውን ምዝገባና ክትትል እንደማያካሂድ ለማወቅ ተችሏል፡፡

124. የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ስለጉዳዩ በሰጡት መልስ ለረጅም ግዜ የክትትል ችግር የነበረ ቢሆንም ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ መረጃዎችን ለማጣራት ጥረት እየተደረገ መሆኑንና ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ የተላለፉትን ዕቃዎች መረጃ ከሞላ ጎደል ለመያዝ የተሞከረ እንደሆነና ከ2003 ዓ.ም በፊት ያሉትን በቀጣይነት የሚሰሩ ገልጸዋል፡፡

125. ከዚህም በተጨማሪ ችግሩ ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ ሲንከባለል የመጣ በመሆኑ ይህን ችግር ለማቃለል ባለስልጣን መ/ቤቱ በ2006 ዓ.ም ባደረገው ክትትል ከጀንአድና አዲስ ፋና ከነበረባቸው ውዝፍ ሂሳብ ውስጥ ብር 253,196,449.58 ገቢ ያደረጉ መሆኑን እንዲሁም በውሉ መሰረት ወለድ ለመጠየቅና ውዝፉን በህግ ለማስከፈል የሚረዱ መረጃዎችን ማሰባሰብ የተጀመረ መሆኑንና በቀጣይም ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እንደሚሰራ ገልጸዋል፡፡

126. ለመከላከያ የሚሸጡ ምግብ ነክ ዕቃዎች ሂሰብን በተመለከተ እንደማንኛውም ገቢ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሰስ የሚደረግ መሆኑን፤

127. እንዲሁም በእያንዳንዳቸው ስም የሂሳብ ቋት ባይከፈትም ሲንከባለል የመጣውን ችግር ለመቅረፍ በእያንዳንዳቸው ስም መረጃዎችን / ምን ያህል እንደወሰደ፣ ምን ያህል እንደተከፈለ እና ምን ያህል እንዳልተከፈለ / በሶፍትና በሀረድ ኮፒ እንዲያዙ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡

128. በሌላ በኩል በኦዲት ቡድኑ ለባለስልጣን መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ከላይ የተገለጹትን ችግሮች አስመልክቶ በ06/01/07 ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ በመጀመሪያ ጊዜ ቅ/ጽ/ቤቶች በዱቤ ሽያጭ የሚያስተላልፉትን የንብረት ሂሳብ ለገቢ አሰባሰብ ዳይሬክቶሬት የሚያሳውቁና ሂሳቡን የሚከታተለው እንደነበር ነገር ግን ከ 2004 ዓ.ም አጋማሽ በኋላ በታክስ ዕዳና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ከተቋቋመ በኋላ በፊት ስለተሰራው መረጃ የሌለ በመሆኑ ትክክለኛውን መረጃ ለማወቅ ያልተቻለና የጠራ መረጃ አለመኖሩን ነገር ግን አሁን መረጃዎቹን ለማሰባሰብ ጥረት እየተደረገ የሚገኝ መሆኑን፤እንዲሁም ጅንአድ ዋጋ ተሰርቶ ከወሰደ በኋላ ዋጋው ችግር አለበት የሚለው ላይ ከመ/ቤቱ ጋር በመነጋገር ስምምነት ላይ እንደተደረሰ ገልጸዋል፡፡

129. የጅንአድ የሥራ ሃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በውሉ መሰረት በ120 ቀን ውስጥ ገቢ እንደማይደረግ ምክንያቱ ደግሞ በአሁኑ ሰዓት ከ 2000 ዓ.ም ጀምሮ ያልተከፈለ ሂሳብ ስለነበረ እሱን እየከፈሉ እንደሆነና እስከ 2004 ዓ.ም ያለውን ሂሳብ መከፈሉን እና የ2005 ዓ.ም አለማለቁን ነገር ግን ባለስልጣን መ/ቤቱ በደብዳቤ የሚያሳውቃቸው ቢሆንም ተፈጻሚ አለመሆኑን በተጨማሪ ውሉ ወለድ መክፈል ይኖርበታል ቢልም ያልከፈሉ መሆኑንና በዋናነት ክፍያቸዎ ያልተፈጸሙት ለዕቃዎች የተጋነነ ዋጋ ስለሚተከል መሆኑን ገልጸዋል ፡፡

130. ይሁንእንጂ ባለስልጣኑ በዱቤ ሽያጭና ለተለያዩ መ/ቤቶች በክፍያ የሚተላለፉ ንብረቶች ሂሳብ የሂሳብ ቋት/ Ledge r/ በመክፈት ሂሳቡበወቅቱ ገቢ እንዲሆን ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ በመሆኑ ትክክለኛውን መረጃ ለማግኘትና የሚፈለገው ሂሳብ በወቅቱ ገቢ ሆኖ ለሚፈለገው አገልግሎት ላይ እንዳይውል አድርጓል፡፡

## በታክስ እዳየተያዙ ንብረቶችን ወደ ገቢ እንዲቀየሩ መደረጉን በተመለከተ

131. በታክስ እዳ የተያዙ ንብረቶችን በመመሪያው መሰረት በወቅቱ ወደ ገቢ የሚቀየሩበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

132. በታክስ ዕዳ የተወረሰ ንብረት ባለንብረቱ ዕዳውን እንዲከፍል ከተነገረበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ውስጥ ክፍያውን ካልፈጸመ ንብረቱ ተሽጦ ዕዳው መከፈል ያለበት ቢሆንም በታክስ እዳ የተወረሱ ንበረቶች መመሪያውን መስረት በማድረግ በወቅቱ ወደ ገቢ እንዲቀየሩ አልተደረጉም፡፡

133. የኦዲት ቡድኑ በናሙና ካያቸው ከአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በ2004 ዓ./ም ግምታቸው 976,684.73 የሆኑ እቃዎች ተወርሰው በ2005 ዓ.ም ለዋናው መ/ቤት የተላለፉ ቢሆንም ወደ ገቢ ያልተቀየሩ መሆኑ እንዲሁም ከአዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤቶች የተወረሱ እና ለዋናው መስሪያ ቤት ከ2004ዓ.ም ጀምሮ የተላለፉ ግምታቸው ብር 269,257,415.8 የሆነ ንበረቶች ተሸጠው ወደ ገቢ እንዲቀየሩ እንዳልተደረገ ታውቋል፡፡

134. የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ስለጉዳዩ በሰጡት መልስ በታክስ ዕዳ የተያዙ ንብረቶችን ለማስወገድ በጨረታ የመሸጥ ሥራ በ2006 ዓ.ም የተጀመረ መሆኑንና በ2007 ዓ.ም በስፋት የሚሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

135. በሌላ በኩል በኦዲት ቡድኑ ለባለስልጣን መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ከላይ የተገለጹትን ችግሮች አስመልክቶ በ06/01/07 ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ ቅ/ጽ/ቤቶች በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን እንዲያስወግዱ መመሪያ የተላለፈ እና በመመሪያው መሰረት ከስራ ሂደቶች የተወጣጣ ቡድን /ቨርቹዋል ቲም/ አቋቁመው እንዲያስወግዱ የተደረገ ሲሆን ነገር ግን በአዲስ አበባ የሚገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች በታክስ ዕዳ

የተያዙ ንብረቶችን ዳይሬክቶሬቱ ከየቅ/ጽ/ቤቶቹ አንድ ላይ ሰብስቦ የሚያስወግዳቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

136. ይሁንእንጂ በታክስ እዳ የሚወረሱ ንበረቶችን ለማስተዳደር እና ለማስወገድ ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ግልጽ የሆነ መመሪያ ስርጭት ባለመኖሩ እንዲሁም ማን ማስተዳደርና ማስወገድ እንዳለበት ማለትም ንብረቶቹን ዋና መስሪያ ቤት ወይም ቅ/ጽ/ቤቶች እንደሚያከናውኑት በግልጽ ያልተቀመጠ በመሆኑ ንብረቶችን ያለመውረስና የተወረሱትንም በወቅቱ በማስወገድ ወደ ገቢ እንዳይቀየሩ ባለመደረጉ የመ/ቤቱን ገቢ በቅልጥፍና እንዳይሰበሰብና ሳይወገዱ የሚቀመጡ ንብረቶችን ለብልሽትንና ለብክነት እንዲጋለጡ አድርጓል፡፡

### በድርድር ያልተሸጡ እቃዎች በጨረታ እንዲሸጥ የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ፣

137. ባለስልጣን መ/ቤቱ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በተለያዩ ምክንያቶች በድርድር ለመግዛት ፈቃደኛ ያልሆኑባቸውን እቃዎች በጨረታ መሸጥ ይኖርበታል፡፡

138. ይሁንእንጂ በባለስልጣን መስሪቤቱ በተለያዩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የመንግስት መስሪያቤቶች በዋናነት ጅንአድ አልወሰድ ያለቸው በርካታ ግምት ያለቸው እቃዎች ያሉ ቢሆንም ጨረታ በማውጣት እንዲወገዱ እንዳለደረገ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

139. በባለስልጣን መ/ቤቱ አዲስ አበባ ቃሊቲ፣ አዳማ፣ ድሬደዋ ፣ ሚሌ ፣ ጅጅጋ፣ ሞያሌ ፣ ባህርዳር ፣ ኮምቦልቻ ባሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በዋናነት ጅንአድ እና ሌሎች መ/ቤቶች አልወሰድ ያሉዋቸው ግምታቸው የማይታወቅና የተጠናቀረ መረጃ የሌላቸው ዕቃዎች ያሉ ሲሆን በተለይ በአዲስ አበባ ኤርፖርት ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ የተከማቹ ከፍተኛ ግምት ያላቸው ኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች የተለያየ ሞዴል ያላቸው የሞባይል ቀፎዎች እና ሌሎች ዕቃዎች በጨረታ እንዲወገዱ አልተደረገም ፡፡

140. ስለ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ሲመልሱ ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ የነበሩ እና የልተወገዱ ዕቃዎች መኖራቸው በግምገማ እና በካል ጉብኝት ታውቆ ሰፊ የማስወገድ ሥራ በሁሉም ቅ/ጸ/ቤች መጀመሩን እንዲሁም በ2007 ዓ.ም አጠናክረው የሚቀጥሉበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

141. ይሁን እንጂ የመንግስት መ/ቤቶች በድርድር ለመግዛት ፈቃደኛ ያልሆኑባቸውን ንብረቶች በመለየት በወቅቱ በጨረታ እንዲሸጡ ባለመደረጉ ዕቃዎቹ ከፍተኛ የሆነ ክምችት የፈጠሩና የመጋዘን ጥበት ያስከተሉ ሲሆን ዕቃዎቹ በወቅቱ በጨረታ ተሸጠው ወደ ገቢ እንዳይቀየሩና ዕቃዎቹ ገበያ ላይ ተፈላጊነታቸው እንዲቀንስ ተጽዕኖ አድርጓል፡፡

### ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በዱቤ የሚሻጣቸውን እቃዎች ዝርዝርና ዋጋ የሚያሳውቅ መሆኑን በተመለከተ

142. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በዱቤ የሚሻጣቸውን የተወረሱ ዕቃዎች ዝርዝርና የሚሸጥበትን ዋጋ ለገዥዎች ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

143. ባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ አዳዲስ እቃዎችን በዱቤ ሽያጭ ለጅንአድና ለአዲስ ፋና የሚያስተላልፍ ሲሆን ነገር ግን በአንዳንድ ቅ/ጽ/ቤቶች የዕቃዎችን ዝርዝር፣ምን ያህል ብዛት እንዳለቸው እና ዋጋቸው ምን ያህል እንደሆነ በማስላት ወጥ በሆነ መልኩ በቅድሚያ ለገዢዎች እንደማያሳውቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

144. በጅንአድና በባለስልጣን መ/ቤቱ መካከል በተደረገው ውል አንቀጽ ሁለት 2.5 መሰረት የዕቃ ዝርዝር እና የሚሸጥበትን ዋጋ በቅድሚያ ለገዢ ማሳወቅ አለበት የሚል ቢሆንም፣ የኦዲት ቡድኑ በናሙና ካያቸው የአዲስ አበባ ኤርፖርት ፣ አዲስ አበባ ቃሊቲ፣ አዳማ ፣ ሚሌ ፣ ድሬደዋ ቅ/ጽ/ቤቶች ቅድሚያ ሰርተው የሚልኩ ሲሆን የጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት በዱቤ ሽያጭ ለጅንአድ የሚተላለፉ የዕቃዎቹን ዝርዝርና የሚሸጥበትን ዋጋ የሚልከው ዕቃው ከተጫነ በኋላ መሆኑ ታውቋል፡፡

145. እንዲሁም የጅንአድ የስራ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ አብዛኛውን ጊዜ የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ከቃሊቲ እና ከቦሌ ጉምሩክ በስተቀር የዕቃ ዝርዝር እና ዋጋ የማይልኩላቸው መሆኑንና አብዛኛውን ጊዜ ዕቀዎች እንድንረከብ የምንደረገው በስልክ መልዕክት ሆኖ ዕቃው ከተጫነ በኋላ የሰነድ እና የዋጋ ትመና ስራ እንደሚካሄድና በዚህም ምክንያት አብዛኛው የተረከብናቸው ዕቃዎቹ የማይሸጡ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

146. የባለስልጣኑ የበላይ ሃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ሲመልሱ በጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤት ችግሩ መኖሩን ታውቆ አሁን የተስተካከለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

147. ይሁን እንጂ ባለስልጣን መ/ቤቱ በዱቤ የሚሸጣቸውን የተወረሱ ዕቃዎች ዝርዝር መረጃ እና የሚሸጥበትን ዋጋ በቅድሚያ ለገዢው የማያሳውቅ በመሆኑ በገዢና ሻጭ መካከል በውል ስምምነት መሰረት ክፍያ በወቅቱ እንዳይፈጸምና በተገለጸው ዋጋ ላይ አለመግባባትና ተጨማሪ ጊዜና ወጪ እንዲያስከትል ያደርገዋል፡፡

## መ/ ባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶቸ አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድ ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዐት መዘርጋቱና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፣

### ከባለ ድርሻ አካላት ጋር የሚሰራበት ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱንና የመግባቢያ ሰነድ ያለው መሆኑን በተመለከተ

148. ባለስልጣን መ/ቤቱ ከበለድርሻ አካላት ጋር በቅንጀት የሚሰራበት ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርአት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግና የመግባቢያ ሰነድ ሊኖረው ይገባል፡፡

149. በባለስልጣን መ/ቤቱ በጉሙሩክ እና በታክስ እዳ የተወረሱ ንብረቶችን ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠበቅና ለማስወገድ እንደ ንብረቶቹ አይነትና ባህሪ ከባለድርሻ አካላት ጋር ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ በቅንጅት የሚሰራበት ሁኔታ የሌለ እና በዚህ ዙርያ ከሚመለከታቸው ከጅንአድና እና ከአዲስ ፋና በስተቀር ከጤና ጥበቃ፣ ከጤና ስነ ምግብ ክብካቤ ባለስልጣን፣ ከቅርስ ፣ከመከላከያ እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ እንደሌለው በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

150. ስለ ሁኔታ የባለስልጣኑ የበላይ ሀላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ሲመልሱ ባለሰልጣኑ የመገበቢየ ሰነድ የለውምነገር ግን ከመድኋኒት ቁጥጥር ባለሰልጣን መ/ቤተ ጋርበቅንጅት የሚሰራ መሆኑን እና ከሌሎቹ ጋር በ2007 ዓ.ም የሚፈጸም መሆኑን ገልጸዋል፡፡

151. ባለስልጣኑ የተወረሱ ዕቃዎችን እንደ ዓይነትና ባህሪያቸው ለማስወገድ ከሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካለት ጋር በቅንጅት ባለመስራቱ እና የመግባቢያ ሰነድ ሌለው በመሆኑዕቃዎች ተከማችተው እንዲቀመጡ፣ በወቅቱ ወደ ገቢ እንዳይቀየሩ፣ አገልግሎት ላይ እንዳይወሉና በአከባቢና በማህበረሰቡ ላይ ጉዳት እንዲያስከትል ሊያደርግ ይችላል፡፡

### ከአዲስ አበባ ውጪ እና አዲስ አበባ የሚገኙ ተሸከርካሪዎች ለማስወገድ ከሚመለከታቸው ባድርሻ አካላት ጋር አብሮ የሚሰራ መሆኑን በተመለከተ

152. የባለስልጣን መ/ቤቱ በአዲስ አበባ እና ከአዲስ አበባ ውጪ ያሉ ቅ/ጽ/ቤቶች በታክስ እዳ የተወረሱ ተሸከርካሪዎች ለጨረታ ወይም ለሀራጅ መነሻ ዋጋ የሚሆን የንብረት ዋጋ ግምት ከመንገድ ትራንስፖርት እናአግባብነት ካለቸው የክልል መንግስታት መ/ቤቶች ጋር በትብብር ሊሰራ ይገባል፡፡

153. ባለስልጣን መ/ቤቱ በአዲስ አበባ እና ከአዲስ አበባ ውጪ ባሉ ቅ/ጽ/ቤቶች በታክስ እዳ የተወረሱ ተሸከርካሪዎች በጨረታ ወይም በሀራጅ ተሸጠው ሂሳባቸው በወቅቱ ገቢ እንዲሆን ለማስቻል የመነሻ ዋጋ ለማሰራት ከመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን መ/ቤት እና አግባብነት ካላቸው የክልል መንግስት መ/ቤቶች ጋር ቀልጣፋ እና ውጤታማ ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት እንዳልዘረጋ ለማወቅ ተችሏል፡፡

154. በባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ እዳ የተወረሱ ተሽከርካሪዎች በዋጋ ግምት ምክንያት ሳይወገዱ ለረጅም ግዜ የተቀመጡ ሲሆን ነገር ግን ዋጋ ለማስገመት ከመንገድ ትራንስፖርት ሚንስቴር መ/ቤት ጋር በቅንጅት ስለመስራቱ የሚያሳይ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

155. ከምራብ አዲስ አባባ ፣ ከምስራቅ አዲስ አበባና ከሌሎች በአዲስ አበባ አካባቢ ከሚገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች በታክስ ዕዳ የሚወረሱ ተሽከርካሪዎች ለዋናው መ/ቤት ለተያዙና ለተወረሱ ንብረቶች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ከ 2004 ዓ.ም ጀምሮ እንዲያስወግዳቸው የሚተላለፉ ቢሆንም በወቅቱ ሳይወገዱ ተቀምጠው እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል፡፡

156. ስለ ሁኔታ የባለስልጣኑ የበላይ ሀላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ሲመልሱ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች አሰራሩ የተለመደ ባይሆንም የድሬደዋ ቅ/ጽ/ቤት ከመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን መ/ቤት ጋር እየሰራ የሚገኝ መሆኑንና በ2006 ዓ.ም ዳይሬክቶሬቱ ከተረከባቸው ተሽከርካሪዎች ብዙዎቹ በጨረታ የተሸጡ ሲሆን ቀሪ ተሽከርካሪዎችና ንብረቶችን ለመሸጥ የጨረታ ሰነድ ዝግጅት የተጠናቀቀ መሆኑንና የሌሎች ንብረቶች ደግሞ የዋጋ ግምት እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

157. በመሆኑም የባለስልጣን መ/ቤቱ በአዲስ አበባና ከአዲስ ውጭ ባሉ ቅ/ጽ/ቤቶች በታክስ ዕዳ የተወረሱ ተሽከርካሪዎች ለጨረታ ወይም ለሃራጅ ዋጋ መነሻ የሚሆን የንብረት ዋጋ ግምት ስራ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ የቅንጅት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ባለመድረጉ በርካታ ተሽከርካሪዎች ለረጅም ጊዜያት ሳይወገዱ ተከማችተው እንዲ ቀመጡ በማድረግ የማስቀመጫ ቦታ ጥበት እንዲፈጥሩና ተሽከርካሪዎቹ አገልግሎት ሳይሰጡ ለብልሽት እንዲጋለጡ አድርጓል፡፡

# ክፍልሦስት

## የመደምደሚያ ሃሳቦች

158. በጉምሩክና በታክስ ዕዳ በተወረሱ ንብረቶች አያያዝ ፣አጠባበቅና አወጋገድ ዙሪያ ከተወረሱ ንብረቶች የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለማስገኘት በባለስልጣን መ/ቤቱ ፣ በቅ/ጽ/ቤቶች እና በባለድርሻ አካላት የተደረጉ ጥረቶች መኖራቸውን እንረዳለን፤ ከክዋኔ ኦዲት ዋና ዋና ዓላማዎች አንዱ በመንግስት የሚወጡ አዋጆች እና ደንቦች እንዲሁም በመ/ቤቶች የተዘረጉ የአሰራር ስርአቶች እና የወጡ መመሪያዎች በአግባቡ ተፈፃሚና ውጤታማ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ከዚህ ዓላማ አንፃር የባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶች አያያዝ ፣ አጠባበቅና አወጋገድ አፈጻጸም ውጤታማነት በኦዲቱ በሚገመገምበት ወቅት ከዚህ በታች የተመለከቱ ዋና ዋና የአሠራር ክፍተቶች ታይተዋል፡፡

- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን ለመያዝና ለማስወገድ ዘመናዊ የሆነ የመረጃ አያያዝ ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ እንዲሆን ያላደረገና የመረጃ ቋት/database/ ያላደራጀ በመሆኑ የተወረሱ ንብረቶች መረጃ በተደረጀ መልኩ አልተያዘም፡፡
- ❖ በባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የሚወረሱ ንብረቶች የአመዘጋገብ ስርዓት ያለ ቢሆንም በአሰራር ስርዓቱ መሰረት ተግባራዊ መደረጉን የማይከታተል በመሆኑ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች አንድ ዓይነት ወይም ወጥ የሆነ የአሰራር ስርአት የለም፡፡
- ❖ በዋናው መ/ቤት እና በቅ/ጽ/ቤቶች general ledger እንዲሁም ንብረት በተላለፈላቸው ድርጅቶች ስም ተቀጽላ ሌጀር /subsidary ledger/ ያልተከፈተ በመሆኑ ንብረቶች በተለያየ መንገድ ሲወገዱ ሂሳባቸውን በወቅቱ በመመዝገብ የተከፈለውን እና ያልተከፈለውን ትክክለኛ ቀሪ ሂሳብ በቀላሉ ለማወቅ አሰቸጋሪ እንዲሆን አድርጎታል፡፡
- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ በዋናው መ/ቤት እና በቅ/ጽ/ቤቶች በጉምሩክ እና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን ዓይነት፣ ብዛት እና ያሉበትን ሁኔታ ለማወቅና ለመከታተል ከተለያዩ የሥራ ሂደቶች ባለሙያዎች መርጦ በማዋቀር በየበጀት አመቱ ወጥ በሆነ መልኩ የንብረት ቆጠራ አያደርግም፡፡

- በባለስልጣኑ የተዘጋጀው የዋጋ መተመኛ ዘዴ /ሲዲ/ ወቅታዊ እንዲሆን ባለመደረጉ እና ለባለሙያዎች በወቅቱ  የአቅም ግንባታ እንዲያገኙ ባለማድረጉ ለተወረሱ ንብረቶች የተጋነነ ዋጋ እንዲተመን ፣ በቅ/ጽ/ቤቶች መካከል አንድ ዓይነት መስፈርት ላላቸው ዕቃዎች የተለያየ ዋጋ እንዲተመን እና የተወረሱ ንብረቶች በወቅቱ እንዳይወገዱና ከፍተኛ የንብረት ክምችት እንዲፈጠር አድርጓል፡፡
- ባለስልጣኑ  ከሀገር ሲወጡና ወደ ሀገር ሲገቡ የሚወረሱ የውጭ ሀገር ገንዘቦች እና የከበሩ ማዕድናት በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲወገዱ እና ሂሳባቸው በወቅቱ ገቢ እንዲሆን በቂ ክትትል እና ቁጥጥር ኣላደረገም፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ለመድሀኒት፣ ለምግብ፣ ለአደገኛና ለሌሎች ንብረቶች ትኩረት በመስጠት  እንደ ንብረቶቹ ዓይነትና ባህሪ እስከሚወገዱ ድረስ ሊቆዩ የሚችሉበት የተሟላ መሳሪያ ያለው ዝግና ክፍት መጋዘን እንዲኖር እንዲሁም ንብረቶች ይዞታቸውና መሰረታዊ ባህሪያቸውን ሳይለውጡ ለደህንነታቸው ተስማሚ በሆነ ሆኔታ የተቀመጡ ስለመሆናቸው በቂ ክትትልና ቁጥጥር አላደረገም፡፡
- በለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን በተመለከተ በስትራቴጂክ ዕቅዱ እና በአመታዊ እቅዱ እንዲካተት ያላደረገ በመሆኑ በአፈጻጸም ለሚታዩ  ክፍተቶች ወቅታዊ የመፍትሄ እርምጃ እንዳይወሰድ አድርጎታል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በጉሙሩክ ለተወረሱ ንብረቶች  የአያያዝ/አጠባበቅ መመሪያ ያለወጣ ሲሆን በታክስ ዕዳ ለተወረሱ ንብረቶች ያወጣው የአፈጻጸም መመሪያ የሌላቸው ቅ/ጽ/ቤቶች ያሉ መሆኑ እንዲሁም በመመሪያው አፈጻጸም ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት በወቅቱ እንዲሻሻሉ ያላደረገና ተግባራዊ ስለመደረጉ በቂ ክትትል እና ቁጥጥር በማድረግ የማያረጋግጥ መሆኑ ታውቋል፡፡
- በባለስልጣን መ/ቤቱና በቅ/ጽ/ቤቶች በጉሙሩክና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን ለመያዝ ለመጠበቅና ለማስወገድ  መዋቅሩን መሰረት ያደረገ የተሟላ የሰው ሀይል የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶችን የሚያስወግድ ኮሚቴ ያቋቋመ ቢሆንም አስወጋጅ ኮሚቴው የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በአግባቡ ስለመወጣቱ ወቅታዊ የሆነ ክትትል አያደርግም፡፡
- ባስልጣን መ/ቤቱ ቶሎ የሚበላሹ አደገኛ የሆኑ ንብረቶችን  በሰውና በአከባቢ ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ወዲያውኑ እንዲወገዱ የማያደርግና እንዲሁም  ባለስልጣን መ/ቤቱ ሊያወድም

የማይችላቸውን ንብረቶች ማውደም ለሚችሉ መ/ቤቶች እንዲተላለፉ አስፈላጊውን ክትትል አላደረገም፡፡

- ❖ በባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ እዳ የተያዙ ንብረቶች በመመሪያው መሰረት በወቅቱ ወደ ገቢ እንዲቀየሩ ኣላደረገም፡፡
- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በድርድር ለመግዛት ፈቃደኛ ያልሆኑባቸውን እቃዎች በመለየት መመሪያውን መሰረት በማድረግ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች (ወጥ በሆነ መልኩ) በጨረታ እንዲሸጡ ያላደረገ እና በዱቤ ሽያጭ የሚሸጣቸውን የተወረሱ እቃዎች ዝርዝርና የሚሸጡበትን ዋጋ ወጥነት ባለው መልኩ በቅድሚያ ለገዢው የማያሳውቅ መሆኑ
- ❖ ባለስልጣኑ በዱቤ ሽያጭ ለሚተላለፉ የተወረሱ ንበረቶች ተገቢው ክፍያ በወቅቱ ገቢ ስለመደረጉ አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር አያደርግም፡፡
- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን በወቅቱ ለማስወገድ ከተወሰኑ ባለድርሻ አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ የሌለው መሆኑ፣
- ❖ ባለስልጣኑ በአዲስ አበባ እና ከአዲስ አበባ ውጭ ያሉ ቅ/ጽ/ቤቶች በታክስ ዕዳ የተወረሱ ተሽከርካሪዎች በጨረታ ወይም በሀራጅ ተሸጠው ወደ ገቢ እንዲቀየሩ ዋጋቸውን ለማስገመት ከሚመለከታቸው ባለድርሻአካላት ጋር በቅንጅት የማይሰራ መሆኑ፣

በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶች አያያዝ አጠባበቅና አወጋገድ በብቃት ናውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ እንዳልሆነ ያሳያል፡፡ ይህን መሰረት በማድረግ በሚቀጥለው የሪፖርት ክፍል በኦዲቱ ወቅት የታዩትን የአሰራር ክፍተቶች ለማሻሻል አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ተብሎ የታመንባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

# ክፍልአራት

# የማሻሻያ ሀሳቦች

- ❖ የመረጃ ቴክኖሎጂ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የሚወረሱ ንብረቶችን ለመመዝገብና ለማስወገድ የሚያግዝ ዘመናዊ የሆነ የመረጃ ቴክኖሎጂ ስርዓት በመዘርጋት ስራ ላይ እንዲውል ሊያደርግ እና ስለ እያንዳንዱ የተወረሰ ንብረት የሚገልጽ ሙሉ መረጃ የያዘ የመረጃ ቋት እንዲደራጅ ሊደረግ ይገባል ፡፡
- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ ለተወረሱ ንብረቶች ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የንብረት አመዘጋገብና ሂሳብ አያያዝ ስርዓት ሊዘረጋና በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ወጥ የሆነ የአሰራር ስርዓት እንዲኖር የግንዛቤ ማስጨበጫ በመስጠት አስፈላጊውን ክትትል ሊያደርግ ተግባራዊ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ በጉምሩክ ና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን በተለያየ መንገድ ሲወገዱ ሂሳባቸውን ለመከታተል የሚያስችል General ledger እና subsidary ledger /ተቀጽላ የሂሳብ ቋት ሊከፍት ይገባል፡፡
- ❖ የተወረሱ ንብረቶች በተለያየ መንገድ ሲወገዱ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸውን ከፍ ለማድረግ፣ ለቁጥጥርና ለክትትል አመቺ ይሆን ዘንድ ንብረቶችን በዓይነት፣ በመጠንና በብዛት ተለይተው ተገቢው መረጃ በተሟላ መልኩ መያዙን ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ እና እንዲሁም ንብረቶቹ ለብክነትና ለምዝበራ እንዳይጋለጡ በየበጀት አመቱ ቆጠራ መደረጉን ሊከታተልና የቆጠራ ሪፖርት እንዲቅረብ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶችን ለማስወገድ ያዘጋጀውን የዋጋ መተመኛ ዘዴ /ሲዲ/ በየጊዜው ወቅታዊ ሊያደርግና በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ወጥነት ያለው የዋጋ አተማመን እንዲኖር ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ በተለያዩ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች የሚያዙ የውጭ ሀገር ገንዘቦችን ቅ/ጽ/ቤቶች ለባለስልጣን መ/ቤቱ እንዲያሳውቁና በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ገቢ ስለማድረጋቸው አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚያዙ የከበሩ ማዕድናት በቆይታ መሰረታዊ ይዞታቸውን ሳይለቁ ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ተላልፈው ለሚፈለገው አገልግሎት እንዲውሉ ሊያደረግና በወቅቱ ወደ ገቢ ሊቀየሩ ይገባል፡፡

- ባለስልጣን መ/ቤቱ እስከሚወገዱ ድረስ ለመድሀኒቶች፣ለምግቦች፣ ለአደገኛና ለሌሎች ንብረቶች እንደ ዕቃዎቹ ዓይነትና ባህሪያቸው ተለይተው በሰውና በአከባቢ ላይ ጉዳት እንዳያስከትሉ ተለይተው ሊቀመጡ የሚችሉበትና የተሟላ ግብአት ያለው መጋዘን ሊያዘጋጅ እንዲሁም የተወረሱ እቃዎችን በሕግ ተይዘው ጉዳይ ካለባቸው ዕቃዎች በመለየት ለቁጥጥር አመቺ በሆነ ሁኔታ የተቀመጡ መሆናቸውን ቀጥጥርና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በጉምሩክ እና በታክስ እዳ የተወረሱ ንብረቶች አጠባበቅ እና አወጋገድን በእስትራቴጅክ ዕቅዱ ሊያካትትእንዲሁም ስትራቴጂክ እቅዱን መሰረት አድርጎ ዓመታዊ ዕቅድ ሊያቅድና እና ዕቅዱን ተግባራዊ በማድረግ የዕቅድ ክንውን ሪፖርት በማዘጋጀት በአፈጻጸም ላይ ለሚታዩ ክፍተቶች በወቅቱ የመፍትሄ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ለተወረሱ ንብረቶች አያያዝ/አጠባበቅ መመሪያ ሊያወጣና እንዲሁም በታክስ ዕዳ የተያዙ ንብረቶች ለማስወገድ የወጣውን መመሪያ ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ሊያሰራጭና በወጣው መመሪያ አፈጻጸም ላይ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት እንዲሻሻሉ ሊያደርግ እንዲሁም ተግባራዊ መደረጋቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመያዝ፣ ለመጠበቅና ለማስወገድ መዋቅሩን መሰረት በማድረግ የተሟላ የሰው ሃይል እንዲኖር ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣኑ የንብረት አስወጋጅ ኮሚቴው የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በአግባቡ ስለመወጣቱ የሚያከናወናቸውን ተግባራት፣ የሚያጋጥሙትን ችግሮች በወቅቱ እንዲፈቱ በማድረግ የተወረሱ ንብረቶች በወቅቱ እንዲወገዱ ስለማድረጉ አፈጸጸሙን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ቶሎ የሚበላሹና አደገኛ የሆኑ ንብረቶችን በአከባቢና በማህበረሰቡ ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉ ችግሮችን ትኩረት በመስጠት ወዲያውኑ እንዲወገዱ ሊደረግና፣ ባለስልጣን መ/ቤቱ ሊያወድም የማይችላቸውን ለማውደም ብቁ ከሆኑ መ/ቤቶች ጋር በቅንጅት በመስራት ንብረቶቹ ቶሎ እንዲተላለፉ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ እዳ የሚወረሱ ንብረቶችን በመመሪያው መስረት በወቅቱ ወደ ገቢ በመቀየር ኢኮኖሚያዊ ጥቅማቸውን ማሰደግና የመንግስት ገቢ በወቅቱ እንዲሰበሰብ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የመንግስት መ/ቤቶች በድርድር ለመግዛት ፈቃደኛ ያልሆኑባቸውን ዕቃዎች በመለየት ክምችት ሳይፈጥሩና ይዞታቸውን ሳይለቁ በጨረታ እንዲሸጡ፣ እንዲሁም በዱቤ የሚሸጡትን የተወረሱ ዕቃዎች ክፍያቸውን በወቅቱ ለመሰብሰበ

አለመግባበት እንዳይፈጠር የሚሸጥበትን ዋጋና የእቃውን ዝርዝር በመግለጽ በቅድሚያ ለገዢ ሊያሳውቅ ይገባል፡፡

- በዱቤ ሽያጭ የሚተላለፉ የተወረሱ ንብረቶች ክፍያ የሂሳብ ቋት እንዲኖር ሊያደርግና በውሉ መሰረት ገቢ መደረጉን አስፈላጊውን ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣኑ በጉምሩክና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን እንደ ዕቃዎች አይነትና ባህሪቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማስወገድ ከሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ ሊኖረው፣ በታክስ ዕዳ የተወረሱ በአዲስ አበባና ከአዲስ አበባ ውጪ የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን በጨረታ/በሀራጅ ለመሸጥ የዋጋ ግምት ለማሰራት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡

በመጨረሻም ለኦዲት ሥራው መሳካት የባለስልጣኑ የዋና መ/ቤት እና ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የስራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ላደረጉልን የስራ ትብብር እና መሰግናለን፡፡

# አባሪ 1፡ የመመዘኛመስፈርት

| የኦዲትጭብጥ<br>Audit issue) | የመመዘኛመስፈርት<br>(Evaluative criteria) |
|---|---|
| 1.የተወረሱ ንብረቶች መረጃ አያያዝ (አመዘጋገብ፣ የሂሳብ ቀልጣፋና ውጤታማ ስለመሆኑ ማረጋገጥ | 1.የባለስልጣኑ የመረጃ ቴክኖሎጂ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት በጉሙሩክና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶች ለመመዝገብና ለማስወገድ የሚያግዝ ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓትሊዘረጋ፣ የአሰራር ስርዓትን መደገፍ የሚያስችሉ ፕሮግራሞችና ሶፍትዌሮች በማበልጸግ ስራ ላይ ማዋል ይጠበቅበታል፡፡ |
| | 2..የባለስልጣኑ የመረጃ ቴክኖሎጂ የስራ አመራር ዳይሬክቶሬት በጉሙሩክና በታክስ የተወረሱ ንብረቶችን አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ የመረጃ ቋት ( data base)ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| | 3..ባለስልጣንመ/ቤቱ በታክስ ዕዳና በጉሙሩክ የተወረሱ ንብረቶች ወደ መጋዘን ሲገቡ እና በተለያየ ስልት ሲወገዱ ተገቢውንመረጃእናማስረጃለመስጠትየሚያስችልቀልጣፋእናውጤታማየንብረትአመዘጋገብእናሂሳብአያያዝስርዓትሊዘረጋእናተግባራዊሊያደርግይገባል፡፡ |
| | 4.በባለስልጣንመ/ቤቱ በታክስ ዕዳና በጉሙሩክ የተወረሱ ንብረቶችን ከተለያየ የስራ ሂደት ባለሙያዎች መርጦ በማዋቀር በየበጀት አመቱ የንብረት ቆጠራ እንዲደረግ እና ሪፐርት እንዲቀርብ ሊያደረግ ይገባል፡፡ |
| | 5..በባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረትቶች በዱቤ የሚሸጡ፣ ለሌሎች መ/ቤቶች የሚተላለፉ፣ በጨረታ የሚሸጡና በማውደም የሚወገትን በዓይነት፣በመጠንና በብዛት በመለየት ተገቢው መረጃ በአግባቡ መያዙን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 6..በባለስልጣኑ የተዘጋጀው የዋጋ መተመኛ ዘዴ /ሲዲ/ ወቅታዊ ሊሆን እና በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ወጥነት ያለው ዋጋ ሊተመን ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | 7..የንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ የንብረት አወጋገድንና የኮሚቴውን አጠቃላይ እንቅስቃሴ በተመለከተ ለበላይ ኃላፊው በየወሩ ሪፖርት ሊያቀርብ ይገባል፡፡ |
| 2.በባለስልጣኑ የተወረሱ ንብረቶች አያያዝና አጠባበቅ ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋና ብቃት ባለው መልኩ ስለማድረጉ መገምገም፣ | 8.. በቅ/ጽ/ቤቶች የሚወረሱ የውጭ አገር ገንዘቦች በ48 ሰዓት ውስጥ ለባለስልጣኑ ገቢ መደረጋቸውን ክትትልናቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 9..በባለስልጣን መ/ቤቱ .ለተወረሱ ንብረቶች ለመድሀኒት ፣ለምግብ፣ለአደገኛና ለሌሎች ዕቃዎች እንደባህሪያቸው ለማቆየት የሚችል የተሟላ መሳሪያ ያለው ልዩ ዝግ መጋዘን ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 10..በባለስልጣንመ/ቤቱመጋዘንውስጥያሉንብረቶችይዞታቸውናመሰረታዊባህሪያቸውሳይለወጥተ ጠብቀውመቆየታቸውበሚያረጋግጥመልኩሊያዙይገባል፡፡ |
| | 11..ባለስልጣን መ/ቤቱየተወረሱ ንብረቶች ወደ መጋዘን ሲገቡ እንደ አይነታቸውና ባህሪያቸው ተለይተው ለደህንነታቸው ተስማሚና ለቁጥጥር አመቺ በሆነ ሁኔታ የተቀመጡ መሆናቸውን ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 12..ባለስልጣን መ/ቤቱ በጉሙሩክ እና በታክስ እዳ ለሚወረሱ ንብረቶች አያያዝ ፣ አጠባበቅ እና አወጋገድ እስትራቴጅክ ዕቅድ ሊያዘጋጅ ፣ አስትራቴጂክ እቅዱን መሰረት አድርጎ ዓመታዊ ዕቅድ ሊያዘጋጅና ዕቅዱን ተግባራዊ በማድረግ የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ሊያቀርብ ይገባል፡፡ |
| | 13..ባለስልጣን መ/ቤቱ በጉሙሩክ እና በታክስ እዳ ለሚወረሱ ንብረቶች አያያዝ ፣ አጠባበቅ ና አወጋገድ እቅድ ክንውን ላይ ለሚታዩ ክፍተቶች ምክኒያታቸውን በመለየት የመፍትሄ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ |
| | 14..ባለስልጣን መ/ቤቱ የመቋቋሚያ አዋጁን መሰረት በማድረግ የአፈጻጸም መመሪያ ለያወጣ፣ ለቅ/ጽ/ቤቶች ሊያሰራጭ እና ተግባራዊ መደረጉን ሊያረጋግጥ እንዲሁም በአፈጻጸም ላይ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት እንዲሻሻል ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 15..በባለስልጣን መ/ቤቱ እና በቅ/ጽ ቤቶች በጉሙሩክ እና በታክስ እዳ የተወረሱ ንብረቶችን ለማስተዳደር የሚያስችል መዋቅሩን መሰረት ያደረገ የተሟላ የሰው ሃይል ሊኖረው ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| 3..በባለስልጣኑ መወገድ የሚገባቸው የተወረሱ ንብረቶች የአወጋገድ ስርዓት ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋና ብቃት ያለው ስለመሆኑ መገምገም | 16..ባለስልጣንመ/ቤቱቶሎሊበላሹለሚችሉንብረቶችንበባለሙያወዲያውኑዋጋእንዲተመንላቸው ሊያደርግይገባል፡፡ |
| | 17..በበለስልጣን መ/ቤቱ በቁጥጥር ስር ያለ ወርቅ እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ ለብሄራዊ ባንክ ሊተላለፍ ይገባል፡፡ |
| | 18.በቅ/ጽ/ቤቶች የተያዙ የከበሩ ማዕድናት እንደተያዙ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ገቢ ሊደርግ ይገባል፡፡ . |
| | 19.በባለስልጣን መ/ቤቱ በጉሙሩክ የተወረሱ ንብረቶችን የሚያስወግድ ኮሚቴ ሊቋቋም እና አፈጻጸሙን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 20..ቶሎየሚበላሹዕቃዎች፣ የቁምእንስሳትናአደገኛየሆኑየተወረሱንብረቶችንወዲያውኑሊወገዱይገባል፡፡ |
| | 21.በባለስልጣንመ/ቤቱሊወድሙየማይችሉአደገኛወይምየተከለከሉዕቃዎችለማውደምብቁለሆኑ መ/ቤቶችሊያስተላልፍይገባል፡፡ |
| | 22..ባለስልጣን መ/ቤቱ በሽያጭ ለሚተላለፉ ወይም ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች በክፍያ ለሚረከቧቸው ዕቃዎች ተገቢውን ክፍያ ለባለስልጣኑ ገቢ መደረጉን ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ |
| | 23..በታክስ እዳ የተያዙ ንብረቶችን በመመሪያውን መሰረት በወቅቱ ወደ ገቢ የሚቀየሩበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡ |
| | 24.ባለስልጣን መስሪያቤቱ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በተለያዩ ምክንያቶች በድርድር ለመግዛት ፈቃደኛ ያልሆኑባቸውን እቃዎች በጨረታ መሸጥ ይኖርበታል፡፡ |
| | 25.በባለስልጣን መ/ቤቱ የዕቃ አስወጋጅ ኮሚቴ የንብረት አወጋገድንና በተመለከተ ቃለ ጉባኤ ሊይዝ ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | 26..ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በዱቤ የሚሻጣቸውን የተወረሱ እቃዎች ዝርዝርና የሚሸጥበትን ዋጋ ለገዥ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ |
| .ባለስልጣን መ/ቤቱ በጉሙሩክ የተወረሱ ንብረቶቸ አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድን በተመለከተ ከበለድርሻ አካላት ጋር በቅንጀት የሚሰራበት ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርዐትና የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑንመገ መገም | 27.ባለስልጣን መ/ቤቱ በተወረሱ ንብረቶች አጠባበቅና አወጋገድ ዙሪያ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ የሆነ ትስስር ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| | 28..ባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶችን እንደ ዕቃዎች አይነትና ባህሪ ከሚያስወግዱ ባለድርሻ አካላት ጋር የመግቢያቢያ ሰነድ ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| | 29..የባለስልጣን መ/ቤቱ ከአዲስ አበባ ውጪ ያሉ ቅ/ጽ/ቤቶች በታክስ እዳ የተወረሱ ተሸከርካሪዎች ለጨረታ ወይም ለሀራጅ መነሻ ዋጋ የሚሆነው የንብረት ዋጋ ግምት አግባብነት ካለቸው የክልል መንግስት መ/ቤቶች ጋር በትብበር ሊሰራ ይገባል፡፡ |
| | 30..የባለስልጣን መ/ቤቱ በአዲስ አበባ የሚገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች በታክስ እዳ የተያዙ ተሸከርካሪዎች በጨረታ ወይም በሀራጅ ተሸጠው በወቅቱ ገቢ ለማስገባት ከትራንስፖርት ሚኒስቴር የዋጋ ገማች በመጠየቅ ሊሰራና አፈጻጸሙን ሊከታተል ይገባል፡፡ |